

እንጀራ ከመሬት ውስጥ ይወጣል (ኢዮ፡ 28፡5)

# ትንሣኤ



ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ

ቁጥር ፳፮ ሐምሌ ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

''ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ ''ትንሣኤ'' ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ም/አዘጋጅ ራደ አስረስ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

# ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ''የእርሻውን ቡቃያ አበዛለሁ'' | ፪ |
| ሥላሴ በቤተ አብርሃም | ፬ |
| የደሴ ከተማ መንፈሳውያን ወጣቶች | ፯ |
| ከሞት በኋላ የሕይወት ታሪክ | ፰ |
| ምን እንርዳዎ ? | ፲ |
| የቅዱሳት አንስት ቅዱስ አገልግሎት | ፲፪ |
| ክርስቲያናዊ ጋብቻ | ፲፬ |
| ሞትን የማይፈሩ | ፲፭ |
| ኅብረተ ሰብእና ባሕል | ፲፯ |
| ዜና ሊቃውንት | ፲፰ |
| የቤተ ሰብእ ዓምድ | ፳ |
| ይህን ያውቁ ኖረዋል ? | ፳፩ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፳፫ |

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

1ኛ/ በግንቦት ወር 1973 ዓ.ም. በታተመው ትንሣኤ መጽሔት ላይ አቶ ተሾመ ካሣሁን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እየተባዛ ለምን አይሰጥም በማለት ጠይቀው መልሱም ከፈለጉ አንድ የተዘጋጀ ሺት እንፈልግልዎት አለን ተብሎ ተመልሶላቸዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሀዶ ቤተ ክርስቲያን የግዕዝና የአማርኛ ማፍለቂያ እንደመሆንዋ ሁሉ ''ሺት'' ለሚለው ቃል እንዴት መጠርያ (ወይም ተመሳሳይ) አጣች?

2ኛ/ አሁንም አቶ ተሾመ ካሣሁን በጾም ወቅት ዓሣ መብላት ይፈቀዳል ወይስ አይፈቀድም በማለት ጠይቀው ፍትሐ ነገሥት ነጠላ ትርጉሙ ይበላል ሲል አንድምታው ግን አይበላም ይላል በማለት መልስ ተሰጥተዋል ።

መልሱ የተብራራ ሆኖ ስላልታየኝ ደግሞ ለመጠየቅ ተገድጀአለሁ ትክክለኛው ነጠላ ትርጉሙነው ወይስ አንድምታው ይብራራ እላለሁ ።

3ኛ/ ዐርባ ጾምን ስንጾም ቆይተን በመፍቻው ወቅት ማለት ከቅዳሜ ስዑር ማምሻው በኋላ ማረድ ይገባል ወይ ? (ወይም ማረድ የሚገባ ከስንት ሰዓት በኋላ) ነው ?

4ኛ ረቡዕና ዓርብ ተጨማሪ ካልኖረው በቀር ሁለት ቀን ገሐድ ነው ተብሎ መጾም መንፈሳዊ ሕግ ነው ወይ ?

ከበረከተ አብ ገ/ መድህን
አ/ አበባ

በረከተ አብ ገብረ መድኅን ስለ ጥያቄዎ እናመሰግናለን ፡ ጥያቄውን ተመልክተነዋል በጥያቄው እንደጠቆሙት ቤተ ክርስቲያናችን የግእዝና የአማርኛ ቋንቋ ባለቤት እንደመሆንዋ ''ሺት'' ለሚለው ቃል ትርጉም አታጣለትም ወረቀት ወይም ልፋፍ በሚለው ልትተረጉመው ትችላለች ግን የዘመኑ ትውልድ የለመደው ቃል ስለሆነና ቋንቋዎችም ሁሉ በራሳቸው ቃላት ብቻ ተወስነው ስለማይኖሩ የአንዱ ቋንቋ ቃል ከሌላው ጋር ተቀላቅሎ ቢነገር አያስነውርም ።

2ኛ/ በጾም ወቅት ዓሣ ይበላል ወይስ ይከለከላል ? ስለተባለው ጥያቄ መልሱ አልተብራራምና ይብራራ ለሚሉት የፍትሐ ነገሥቱ ውሳኔ ይህ ነው ''ወበእሉ አጽዋም እለ ተሠርዐ ይጹሙ እስከ ተሰዓቱ ሰዓት እምዕለት ወኢይበልዑ በሙ ሥጋ ዘእንበለ ዓሣ ፡ በአማርኛ በእነዚህ በታዘዙት ጾሞች ከቀኑ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ይጹሙ ከዓሣ በቀር ሥጋ አይብሉባቸው ።'' ሲል አንድምታው ትርጉም ግን ''ዘእንበላ ዓሣ'' የሚለውን ዓሣ ሳይቀር አይብሉባቸው ይላል ''ዘእንበለ''የተሰኘው አገባብ የተለያየ ትርጉም ስላለው ሊቃውንቱ ይከራከሩበታል ። ታዲያ ነገሩ አከራካሪ ከሆነ አለመብላቱ ይሻላል ምክንያቱም በጾሙ ምክንያት ጠብ ክርክር ቢሆን መጾም ይገባል ። ከመብላት መጦም በጣም ይሻላል'' ተብሎ በዚሁ ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 15 ቁ. 580 ተወስኖአልና።

3ኛ/ የቅዳም ስኡር ዕለት ገና ጾም ሳይፈታ ማረድ አይገባም ማረድ የሚገባው ቅዳሴ ከወጡ በኋላ ሲፈሰክ ብቻ ነው ።

4ኛ/ ገሃድ ሁለት ቀን አይደለም አንድ ቀን ብቻ ነው የልደትና የጥምቀት ዋዜማ አንዳንድ ቀንብቻ የገሃድ ጾም ይጾማል ።



በኢየሩሳሌም ከሚገኙት ቅርሶቻችን አንዱ ይህ ነው ። ሌሎችንም በዝርዝር ለማወቅ የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት በ1973 ዓ.ም ያሳተመውን « የቅዱሳት መካናት መስተዋት የተባለውን መጽሐፍ ያንብቡ ፡ መጽሐፉን ከፈለጉት ስልክ ቁጥር 11 - 91 50 አ.አ ደውለው ይጠይቁ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# "የእርሻውን ቡቃያ አበዛለሁ"

ምድር የሚዘራባትንና የሚተከልባትን እንድታበቅል መለስለስና እርሻ መሆን አለባት ከታረሰችና ከለሰለሰች በኋላ ደግሞ አየር ፣ የፀሐይ ብርሃንና ዝናም ያስፈልጓታል ። "ሰማይ ዝናምን ይሰጣል ምድርም ቡቃያን ታበቅላለች" በሚል ጽኑዕ ተስፋ ገበሬዎች ደረቁን መሬት ያርሳሉ ያለሰልሳሉ ፣ በፀሐያማው በጋ ለሚመጣው ማረስ ፣ ባለፈው ክረምት ተዘርቶ የታጨደውንና የተከመረውን ማምረት የትጉሃን ገበሬዎች የዘወትር ተግባር ነው ።

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በየዕለቱ ከሚለግሣቸው በረከቶች አንዱ ዝናም ነው ገበሬዎችም ይህን አምነው ሜዳውን አርሰው ቁጥቋጦውን አስወግደው ማሳውን አለስልሰው ዘሩን ቋጥረው የዝናሙን ወቅት ይጠባበቃሉ እግዚአብሔርም ተፈጥሮን በሚመራበትና በሚሠራበት ሕግ መሠረት ከሰማይ ዝናምን ይሰጣል ። ገበሬዎችም በእምነትና በተስፋ ዘር ይዘራሉ ፣ እግዚአብሔርም ዘሩን ቡቃያ ፣ ቡቃያውን ሰብል ፣ ሰብሉንም ፍሬ በማድረግ የገበሬዎችን ተስፋ እውነት ያደርገዋል ። መሬትን ደጅ ለሚጠኑ ማለት ለሚያርሱ ለሚቆፍሩ ዘር ለሚዘሩና ተክል ለሚተክሉ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል "..... እህልንም እጠራዋለሁ አበዛውማለሁ ረኃብንም አላመጣባችሁም ። ደግሞም የረኃብን ስድብ ከአሕዝብ (ከጠላቶቻችሁ) ዘንድ እንዳትሸከሙ የዛፉን ፍሬና የእርሻውን ቡቃያ አበዛለሁ ።" ሕዝ 36 ፣ 30

ነፋስ ወጀብና በረዶ ያልተቀላቀሉበት ዝናም የምሕረት ዝናም ነውና ቡቃያን ያበዛል ረኃብን ያስወግዳል ። ነፋስ ወጀብና በረዶ የተቀላቀሉበት ዝናም ግን የመዓት ዝናም ነው ። ስለሆነም እንስሳትን ይጐዳል ቡቃያን ያጠፋል ። ረኃብን ያስከትላል ። ስለዚህም ነው ገበሬዎች ሁሉ ዝናሙን ዝናመ ምሕረት አድርግልን' እያሉ የሚጸልዩ ፤ ዕውነተኛና ሰዎች ሁሉ ሊጸልዩት የሚገባ ጸሎት ነው ። የምሕረት ዝናም በዘነመ ቁጥር መሬት ትታደሳለች እንጂ አትጎዳም ወጀብና በረዶ የተቀላቀሉበት የመዓት ዝናም ሲዘንም ግን ምድር ትጐዳለች በውስጥዋና በላይዋ ያሉት ሁሉ ይጠፋሉ ።

በምድር ላይ የምሕረት ዝናም እንዲዘንም ቡቃያው ሰብል ሰብሉም ፍሬ እንዲሆን ወይም ሰማይ ዝናም ለዘር ጠል ለመከር እንዲሰጥ ምድርም ፍሬዋን እንድታበረክት ሰዎች በሕግና በሥርዓት ጸንተው ባለጸጋው ድኃውን ፣ ኃይለኛው ደካማውን ሳይጫኑውና ሳይገፉው በእኩልነት መኖር አለባቸው ከዚህም ጋር ተፈጥሮን በሥርዓት የሚመራውንና ሁሉን ማድረግ የሚችለውን እግዚአብሔርን በባዕድ አምልኮት አለማስቀናት ነው ። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል "....እናንተ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ትወድዱ ዘንድ በፍጹም ልባችሁ በፍጹምም ነፍሳችሁ ታመልኩት ዘንድ ዛሬ ለእናንተ የማዝዘውን ትእዛዜን ፈጽማችሁ ብትሰሙ እህልህን ፣ ወይንህንም ፣ ዘይትህንም ፣ ትሰበስብ ዘንድ በየጊዜው የበልጉንና የክረምቱን ዝናም ለምድራችሁ አወርዳለሁ ። በሜዳ ለእንስሶችህ ሣርን እሰጣለሁ ። ትበላማለህ ትጠግብማለህ ። ልባችሁ እንዳይስት ፈቀቅ እንዳትሉ ሌሎችንም አማልክት እንዳታመልኩ እንዳትሰግዱላቸውም ፣ የእግዚአብሔርም ቁጣ እንዳይነድድባችሁ ፣ ዝናም እንዳይዘንም ምድሪቱም ፍሬዋን እንዳትሰጥ ሰማይን እንዳይዘጋባችሁ እግዚአብሔርም ከሚሰጣችሁ ከለምለሚቱ ምድር ፈጥናችሁ እንዳትጠፉ ተጠንቀቁ » ዘዳ 11 ፣ 13 - 17 እዚህ ላይ ሊስተዋል የሚገባው ነገር የሰዎች በሕግና በሥርዓት ጸንቶ አለመኖር ከእግዚአብሔር ለሰዎች የሚሰጠውን በረከት የሚከለክል መሆኑን ነው ፣ ከዚህም ሌላ የእርሻውን ቡቃያ የሚያበዛው የበልጉና የክረምቱ ዝናም በየጊዜው መገኘት ብቻ አይደለም ዝናም ሲጥል ዘር ለመዝራት የበጋውን ሐሩር ታግሦ ጓሉን መከስከስ ማሳውን ማለስለስ በክረምቱ ጭቃውን ብርዱንና ዶፉን ሳይሰቀቁ መዝራትና ማረም ነው ።

ጉልበቱንና ዘሩን ለመሬት ያበደረ በአንድዋ ቅንጣት ሠላሳ ፣ ስልሳና መቶ ቅንጣት እጽፍ ድርብአድርጐ ይቀበላል ዘሩን የበላና ጉልበቱን ያሰነፈ ግን ይራባል ፣ ዛሬ ተቸገርን ተራብን የሚሉ ሁሉ ቀበቶአቸውን ጠበቅ አድርገው ምድርን ደጅ ቢጠኑ (ቢያርሱና ቢዘሩ) ነገ ይጠግባሉ "እንጀራ ከምድር ውስጥ ይወጣል" ተብሎ ተጽፎአልና ኢዮ 28 ፣ 5

በተለይ የኢትዮጵያ ምድር ውስጥዋም ላይዋም እንጀራ የተሞላ በመሆኑ "የዳቦ ቅርጫት" የሚል ይች ስያሜ አላት በአይነት የተለያየ ይሁን እንጂ በየትኛውም የኢትዮጵያ ምድር እህል ሊዘራ ተክል ሊተከል ይችላል ኢትዮጵያ በኮረብታዋ ልምላሜ፣በሸለቆዋ ውሃ፣የማይታጣ፣በሰማይ ዝናም የምትረካ፣ወቶችን እየ ላል ኢትዮጵያ በኮረብታዋ ልምላሜ የማጠበቀ እግዚአብሔር በበልግ ዝናም የሚጐበኛት፣ከዓመቱመጀመሪያእስከዓመቱመጨረሻ ልምላሜ የማ ጠበቀ እግዚአብሔር በበልግ ዝናም የሚጐበኛት እን ይለያት በተፈጥሮ የበለጸገች ብትሆንም እስከ አሁን ድረስ እኛ ልጆችዋ እንጀራዋን አልጠገብንም እን ዴት ? የተባለ እንደሆነ ቀደም ሲል በነበረው አስተዳደር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ባለመሬት አልነበረም ፤ ባለመሬቱም ከምድሩ እንጀራውን አውጥቶ ሲበላ ምድር የሌለው ጦሙን ያድር ነበር ። ዛሬስ ? ዛሬማ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና እንደ ኅብረተሰብአዊነት ፍልስፍና ምድር ለሁሉ (ለአራሽዋ) ናት ። ስለዚህ በምድር ውስጥ የሚገኘውን እንጀራ በቡቃያ አማካይነት አውጥቶ ለመብላትና ከረኃብ ለመዳን የበልጉንና የክረምቱን ዝናም ጠብቆ ዘር ለመዝራት የማይተጋ ራሱን በራሱ ያስርባል ። "የዛፉን ፍሬና የእርሻውን ቡቃያ አበዛ ለሁ በማለት የተናገረውን የእግዚአብሔርን በረከት በሰፊው ለመቀበል ሰዎች ማረስ መቆፈርና መዝራት አለ ባቸው በረከት ያለ ሥራ አይገኝምና ። በእርግጥ በሰዎች ሥራ የማይገኝ ሰዎች በተስፋ የሚጠብቁት ከእግዚ. አብሔር ብቻ የሚገኝ ልዩ በረከት አለ እርሱም ዝናም ለዘር ጠል ለመከር ነው ። ታዲያ ዝናምን ለዘር ጠልን ለመከር ስጠኝ" ብሎ የሚጸልይ ሁሉ የጸሎቱ መልስ የሚሆነውን ቡቃያን ፣ ሰብልንና ፍሬን ለማየት እንዲችል መሥራት አለበት ።





www.ethiopianorthodox.org

# ሥላሴ በቤተ አብርሃም



ሥላሴ ሦስትነት ማለት ነው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በአንድነት ሥላሴ ተብለው ይጠራሉ ዓለም ሳይፈጠር ዘመን ሳይቆጠር ሥላሴ እንደ አሁኑ ጊዜ በሦስትነትና በአንድነት ይመስገኑ ነበር የሚመሰገኑትም በፍጡራን አንደበት ሳይሆን ምስጋና የባህርይ ገንዘባቸው ስለሆነ ነው ። ይህም በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ 17 በቁጥር አምስት "አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ምስጋና አንተ በራስህ ዘንድ አመስግነኝ" በማለት ተገልጿል

ይህንን አምላካዊ ቃል መሠረት በማድረግ ዮሐንስ አፈ ወርቅ "ስብሐቲሁ ዘእምኀቤሁ ወውዳሴሁ እምዚአሁ ምሉዕ ወፍጹም ብዕለ ጸጋሁ እምኀበ አቡሁ ተሰብሐ ወእምኀቤሁ ተቀደሰ በማለት ተናግሯል ወደ አማርኛ ሲተረጐም ምስጋናው ከእርሱ የተገኘ ነው ውዳሴው የራሱ ነው ስጦታውም የመላ ነው በአባቱ ዘንድ ተመሰገነ በራሱም ተቀደሰ ማለት ነው ።

በቀሌምንጦስም "ከፈጠርነው ፍጥረት መመስገንን የምንሻ አይደለንም ምስጋናችን የባሕርያችን ነው" ብለዋል ነገር ግን ሥላሴ ዓለምን እንፍጠር ብለው አስበው ዓለምን ከፈጠሩ በኋላ በዓለሙ ላይ ሰውንና መላእክትን ስማቸውን ለመቀደስ ክብራቸውን ለመሥረስ ሲፈጥሩ የቀረውን ፍጥረት ለአንክሮ ለተዘክሮ ለምግበ ሥጋና ለምግበ ነፍስ ፈጥረዋል ። አብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልባቸው ነው ፣ ወልድም ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው መንፈስ ቅዱስም ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው ነው ።

እንግዲህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው በመጠኑ የሥላሴን ሦስትነት እንድን መለከት ያደርገናል እንዲሁም የሥላሴ የአንድነት ስማቸው እግዚአብሔር፣ አምላክ፣ አዶናይ፣ ፈጣሪ፣ የመሳሰሉት ሲሆኑ የሚነገሩትም በነጠላ ነው አብን በተለየ አካሉ ወላዲ አስራጺ ፣ ወልድን በተለየ አካሉ ተወላዲ መንፈስ ቅዱስን በተለየ አካሉ ሠራጺ ብለን ሦስቱን አንድ ፣ እግዚአብሔር አንድ አምላክ እንላለን እንጂ ሦስት እግዚአብሔር ሦስት አምላክ አንልም ።

ይህንንም ስላልን አንድነታቸው ሦስትነታቸውን አይጠቀልለውም ሦስትነታቸውም አንድነታቸውን አይለያየውም ።

ሥላሴ በስም በግብር በአካል ሦስት ሲሆኑ በባሕርይ በሕልውና በስልጣን በፈቃድ አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም ። ስለዚህም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ይህንን ታምና ለች ታሳምናለች ታስተምራለችቤተ ክ ክርስቲያናችን የሥላሴን በዓል በዓመት ሁለት ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ታከብራለች ይኸውም አንደኛው ጥር ሰባት ቀን ሲሆን ሁለተኛው ሐምሌ ሰባት ቀን ነው በጥር የሚከበርበትን ምክንያት ለሌላ ጊዜ እንተወውና ሐምሌ ሰባት ቀን ስለሚከበረው የሥላሴ በዓል እንመልከት ።

ሐምሌ ሰባት ቀን ሥላሴ በአብርሃም ቤት በእንግድነት ተገኝተው ለአብርሃምና ለሚስቱ ለሣራ የልጃቸውን የይስሐቅን መወለድ ያበሰሩበት ዕለት ነው አብርሃምና ሣራ ልጅ ሳይወልዱ መካኖች ሆነው ብዙ ዘመን ኑረዋል ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚለው ለአብርሃም መቶ ለሣራ ዘጠና ዓመት ሆኖአቸው ነበር ። ዕድሚያቸው ስለገፋ ልጅ የማግኘት ተስፋ አልነበራቸውም ።

አብርሃምና ሣራ ከሁሉም ሥነ ምግባር አብልጠው እንግዳ መቀበልን በጣም ይወዱ ነበር ድርሳነ አብርሃም የተባለው መጽሐፍ እንግዳ ያጡ እንደሆነ የእግዚአብሔርን ማዕድ ያለ እንግዳ አንመገበውም በማለት ጦማቸውን ያድሩ ነበር ይላል ።

ከዕለታት አንድ ቀን በቀትር ጊዜ አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር (ሥላሴ) በመምሬ በወይራ ዛፍ ተገለጡለት ዓይኖቹንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ ወደ ምድርም ሰገደና አቤቱ በፊትህስ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ ባሪያህን አትለፈኝ እለምንሃለሁ ጥቂት ውሃ ይምጣላችሁና እግራችሁን ታጠቡ ከዚህም ዛፍ ሥር እረፉ ቁራሽ እንጀራ ላምጣላችሁና በልታችሁ ትሂዳላችሁ ስለዚህ ወደ ባሪያችሁ መጥታችኋልና አላቸው ።

ሥላሴም እሽ እንቆያለን የፈለግኸውን አድርግ አሉት አብርሃምም ወደ ድንኳኑ ወደ ሣራ ሂዶ ሣራን ምግብ እንድታዘጋጅ ነግሮ እርሱ ወደ መንጋው ሄደና ከመንጋው መካከል የሰባውንና የወፈረውን ወይፈን አርዶ አዘጋጅቶ ለሥላሴ አቀረበ ፣ ሥላሴም ከተመገቡ በኋላ እንደዛሬ የዛሬ ዓመት ወደ አንተ ቤት እንመጣለን ሚስትህ ሣራም ወንድ ልጅ ትወልዳለች አሉት ሣራ ይህንን ቃል ሰምታ ከት ብላ ሳቀች ፈጽመው አርጅተው ስለ ነበር እንዴት አድርጐ ይቻላል በማለት ነው ሥላሴ ግን የሣራን ሣቅ ሰምተው ሣራን ለምን ሣቀች ለመሆኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን አሉ ሣራም ስለፈራች አልሣቅሁም ጌታዬ ስትል ካደች ።

ሥላሴ የማያደርጉትን አይናገሩም የተናገሩትንም አያስቀሩምና በተባለው ዕለት በዓመቷ ሣራ ለአብርሃም ወንድ ልጅን አስገኘች (ወለደችለት) ስሙንም ይስሐቅ ብሎ ሰየመው ትርጓሜውም ይስቃ ማለት ነው ።

እንዲሁም ሰዶምና ገሞራ በበደልና በኃጢአት ገመድ ተተብትበው ታስረው ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ዓይነ ልቡናቸው ታውሮ አንመለስም በማለታቸው ከምድር ገጽ እንዲደመሰሱ በተፈረደባቸው ጊዜ በእነርሱ መካከል ይኖር የነበረውን ጻድቁን ሎጥን ለማዳን ባሰበ ጊዜ እግዚአብሔር መላእክትን የላካቸው በእንግዳ አምሳል ነው ። ኦሪ ዘፍ 18 ፡ 1 - 8 ፡ 19 . 1

እንግዳን መቀበል እንደቀላል ነገር የማይቆጠር ለከፍተኛ ክብር የሚያበቃ ነው ክርስቶስም በመጨረሻው ቀን በመጣ ጊዜ ከሚያቀርባቸው ስድስት ጥያቄዎች አንዱ እንግዳ ብሆን ተቀበላችሁኝ ወይ የሚለው ቃል መሆኑ በቅዱስ ወንጌል ተጽፏል ማቴ 25.35

ሐዋርያው ጳውሎስም "እንግዶችን መቀበልን አትርሱ በዚህ አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን አስተናግደዋል ብሏል ዕብ 13. 2

አብርሃም ሥላሴን በእንግድነት ተቀብሎ በማስተናገዱ "አርከ እግዚአብሔር ፍቁረ እግዚአብሔር" የእግዚአብሔር ወዳጅ የእግዚአብሔር ባለሟል ተብሎ እንደተጠራ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣውንም እንግዳ ተቀብሎ በምግብ በልብስ ፣ በቦታ የሚያስተናግድ ሰው ሁሉ እንደ አብርሃም "የእግዚአብሔር ወዳጅ" የሚለውን ሥያሜ ከሥላሴ ዘንድ ይቀበላል ።

ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ





www.ethiopianorthodox.org

# ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን



ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

## የደሴ ከተማ መንፈሳውያን ወጣቶች

አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባሎች እምነታቸውን ባሕላቸውንና መልካሙን ተግባራቸውን ሁሉ ለልጆቻቸው የማስተላለፍ ግዴታ እንዳለባቸው ያውቃሉ ። ስለሆነም በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግና ሥርዓት መሠረት ፣ ወንዶች ልጆቻቸውን በ40 ሴቶቹን ደግሞ በ80 ቀናቸው እንዲጠመቁ (ክርስትና እንዲነሡ) ከማድረጋቸውም በላይ ጥቂት ከፍ ሲሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን እያስከተሏቸው ይሄዱ ነበር። ይህንንም የሚያደርጉት ወጣቶቹ ባደጉ ቁጥር ስለቤተ ክርስቲያናቸው ጥናት እያደረጉ መንፈሳዊ ስብስባቸው እያዳበረ እንዲሄድና በእግራቸው ተተክተው ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲደግፉ ነው ። ይህም በመሆኑ ወደቤተክርስቲያን በሄዱ ቁጥር ትምህርተ ክርስትናን ከማጥናታቸውና ስለእምነታቸው ከማወቅ አልፈው ቤተ ክርስቲያኒቱን እንዲወዱና ለሕጓ ተገዦች ሆነው ሥርዓቷን እንዲጠብቁ ረድቷቸዋል ።

በአሁኑ ጊዜ ግን በወላጆቻቸው ምግዚትነት ወደቤተ ክርስቲያን ከሚሄዱት ይልቅ ራሳቸው አውቀውና ወደው በገዛ ፈቃዳቸው የሚሄዱት ወጣቶች እየበረከቱ ሄደዋል ። ይህም «እሾህ በእሾህ ይወጣል» እንዲሉ በየቤተ ክርስቲያኑ የሰንበት ትምህርት ቤት ስለተቋቋመ የመንፈሳውያን ወጣቶች መዝሙርና መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ሌሎቹን ወጣቶች ስለሚስባቸው በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ እየተደራጁ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን እንዲያበረክቱ አድርጓቸዋል ።

ይህ ዓይነቱ የወጣቶች መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በአዲስ አበባ ብቻ አልተወሰነም ይልቁንም በየክፍለ ሀገሩ በየአውራጃውና ወረዳው በገጠርም ጭምር በጉልህ የሚታይና እጅግ በሚያስደስት ደረጃ ላይ ነው ። ባለፉት ጊዜያት በአዲስ አበባና በሌሎች ክፍላተ ሀገር ስላሉት መንፈሳውያን ወጣቶች በጋዜጣችንም ሆነ በመጽሔታችን ከመግለጣችንም በላይ በየማኅበራቱ እየተገኘን ትምህርት በመስጠት ወጣቶቹ በመንፈሳዊ ዓላማቸው እንዲበረቱ ከማትጋት አልተቆጠብንም በአሁኑም የወጣቶች ዓምድ ዝግጅታችን በወሎ ክፍለ ሀገር ስላሉት መንፈሳውያን ወጣቶች በዓይን ያየነውንና ጠይቀን የተረዳነው ከሞላ ጎደል ለማቅረብ እንሞክራለን ።

በወሎ ክፍለ ሀገር በደሴ ከተማ ብቻ 8 አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ ከነዚሁ አብያተ ክርስቲያናት በአብዛኞዎቹ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበርና የሰንበት ትቤቶች ተቋቁመዋል ። ከመንፈሳውያን ወጣቶች መካከል በደሴ ደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም የወልድ ዋሕድ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር ሲቀ መንበር የሆነውን ወጣት መንግሥቱ ገብረ ሕይወትን ጠይቀን እንደተረዳነው ከ 1961 - 1965 ዓ.ም ድረስ በደሴ ከተማ በደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለምና በደብረ ቤቴል ሥላሴ አብያተ ክርስቲያናት የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት ተቋቁመው ሲሠሩ እንደነበሩና አሁን ግን በዚያን ጊዜ ከነበሩት አባላት አንድም የሌለ መሆኑን አስረድቶ ከ 1966 ዓ.ም ጀምሮ ግን እንደገና በደሴ ደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም የወልድ ዋሕድ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበርና በቅዱስ መርቆርዮስ የፍሬ ሃይማኖት ወ ማኅበር መመሥረታቸውን ገልጧል ።

እነዚህ ሁለት መንፈሳውያን ማኅበራት ሰኔ 4 ቀን 1969 ዓ.ም. አንድ የጋራ ኮሚቴ በማቋቋም ግምባር ፈጥረው በዚያው ወርና ዓ.ም. በደብረ ሰላም ቅ.ሚካኤል በደብረ ቤቴል ሥላሴ ፣ በመዝገበ ምሕረት ማርያም ፣ በገነተ ጊዮርጊስ ፣ መንበረ ፀሐይ ተክለ ሃይማኖትናበአቅራቢያው በሚገኙት የአውራጃና የወረዳ ከተማዎች መንፈሳውያን ማኅበራትን ማቋቋማቸውንና ከዚያም ጊዜ ጀምሮ እየተጠናከረ መምጣቱን ወጣት መንግሥቱአብራርቷል ።


በዚሁ በደሴ ከተማ የሚገኙት የመን



ፈሳውያን ወጣቶች ማኅበራት ቀደም ሲል ተቋቁሞ በነበረው አጠቃላይ ጉባኤ ሰብሳቢነት በ 3 ሳምንት አንድ ጊዜ በመንበረ ጵጵስናው አዳራሽ እየተገኙ መንፈሳዊ ትምህርት እየተከታተሉ የቆዩ ናቸው ። አሁንም ይህንኑ በመቀጠል ከብፁዕ አቡነ ሣሙኤል የክፍለ ሀገሩ ጳጳስና ፈቃደኛ በሆኑ የቤተ ክህነት መምህራን የሚዘጋጅላቸውን ትምህርት በጋራ በመማር መንፈሳዊ እውቀታቸውን እያዳበሩ ናቸው ። የየማኅበራቱ አባላት መንፈሳዊ ይዘታቸው በጣም ደስ የሚያሰኝና በመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት የታነጹ ናቸው ። ከዚህም የተነሣ ታቦታት በሚነግሡባቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ መዝሙር በመዘመርና በማሸብሸብ ለበዓሉ ከፍተኛ ድምቀት ይሰጣሉ ።

በተለይም በመስቀል ፣ በጥምቀትና በቃና ዘገሊላ በዓል ያሬዳዊ መዝሙር እየዘመሩ ሕዝቡን ከማስደሰታቸውም ሌላ ከብሉያትና ከሐዲሳት የተወጣጡ ጥቅሶችን በጉልህ በመጻፍ ትምህርተ ወንጌልን ለሕዝብ ያስተላልፋሉ መዝሙራቸውም ሆነ አለባበሳቸው በጣም ደስ ይላል ። ለምሳሌ የሀገር ልብስ የለበሱና በዕድሜያቸው ጠንከር ያሉት የየማኅበራቱ አባላት ለብቻቸው ፣ 12 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሕፃናት ለብቻ ሆነው የመለዮ ልብሳቸውን ለብሰው ሳይደክሙ በመዘመር እስከመጨረሻው መቆየታቸው የበለጠ ደስ ይላል ።

ሌላው ደግሞ እጅግ ደስ የሚያሰኘው ካህናቱ ከመንፈሳውያን ወጣቶች ጋር የሚያሳዩት ኅብረት ነው ይህ ትብብር ለወጣቶች የሞራል ድጋፍ ስለሚሆናቸው የበለጠ ያበረታታቸዋል በተለይም ወጣቶቹን በመንፈሳዊ ትምህርት የማሠልጠኑ ተግባር የሀገረ ስብከቱን ሰባክያን ብርቱ ጥረት የሚጠይቅ ነው ። ስለዚህ ሰባክያኑም ሆኑ ካህናቱ እስካሁን ድረስ



ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በደሴ ከተማ ከአራቱ መንፈሳውያን የወጣት ማኅበራት አባላት ጋር ።

ያበረከቱት አስተዋጽኦ በመንፈሳውያን ወጣቶች የተገለጠና በሥራም የተተረጐመ በመሆኑ የሚያስመሰግናቸው ቢሆንም ለወደፊቱ ከዚህ የበለጠ እንክብካቤና ትብብር ማድረግ ይገባቸዋል ።እንላለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ከሞት በኋላ የሕይወት ታሪክ

በመልካም ታሪክ አንፃር መጥፎ ታሪክ አለ ይህም ሲባል በወገናቸው ላይ የደረሰውን ግፍና መከራ ለማቃለል ፤ የባርነትንም ቀንበር ለመስበር ውድ ሕይወታቸውን ሰጥተው ለሀገራቸው ነፃነትና ለሕዝባቸው ደኅንነት መሥዋዕትነትን በሚከፍሉ ጀግኖች ጎን ፈሪ የሆኑና ለወገናቸውም ያልሠሩ የሕይወት ታሪክ የሌላቸው ደግሞ አሉ እንደነዚህ ያሉት እንኳንስ ከሞቱ በኋላ ታሪክ ሊኖራቸው ይቅርና በሕይወትም ሳሉ በቁማቸው የሞቱ ስለሆኑ ታሪካቸውም የሞተ ነው ።

ከሞት በኋላ የሕይወት ታሪክ ያላቸው ግን በሠሩት መልካም ተግባር ፤ በፈጸሙት ተጋድሎ ለትውልድ ባወረሱት የጀግንነት ቅርስ ሕዝቡ ሁሉ ስለሚጠቀምበት ታሪካቸው ሕያው ሆኖ ይኖራል እንዲህ ያሉትንም ጀግኖች ለራሳቸው ሳይሆን ለሕዝብም የኖሩና ለሕዝብም የሞቱ በመሆናቸው ከሞት በኋላ የሕይወት ታሪካቸው ጥሩ ምሳሌና አስተማሪ እየሆነ በየጊዜው የሚነሳውን ትውልድ ለሥራና ለጀግንነት ሲቀሰቅስ ይኖራል ።

በመንፈሳዊው ዓለምም ቢሆን የመከራንና የስቃይን ስንክልክል መንገድ በማለፍና መሥዋዕት ሆኖ በመቅረብ በኃጢአት የመረረውን ዓለም በትምህርታቸው ያጣፈጡ ፤ በክህደት ጨለማ ውስጥ ለነበረው ሕዝብ የወንጌልን ብርሃን ያበሩ በኃጢአትም ምድረ በዳ ለሚቅበዘበዘው መንገደኛ ሁሉ ወደ ክርስቶስ የሚወስደውን እውነተኛ መንገድ ያሳዩ ብዙ የመንፈስ ጀግኖችና የሥራ ሐዋርያት ነበሩ ። ከነዚህም መካከል ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ ይገኙበታል ቅዱስ ጴጥሮስ አሣ አጥማጅ ነበር ክርስቶስም “ ሰው አጥማጅ አደርግሃለሁ” ሲል ለደቀ መዝሙርነት መርጦ እንዲከተለው ጠራው ቅዱስ ጴጥሮስም ለስብከተ ወንጌል የተጠራው የሃምሳ ሰባት ዓመት አዛውንት በነበረበት ጊዜ ነው ።



ቅዱስ ጴጥሮስ ቁልቁሊት የሚሰቀልበትን የዕፅ መስቀል እንደ ተሸከመ



ቅዱስ ጳውሎስም ክርስቲያኖችን ለማሳደድ በሚጓዝበት ወቅት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሶርያ ዋና ከተማ በደማስቆ ተገለጸለት“ ስሜን ተሸክመህ ለአህዛብ ሁሉ ታደርስ ዘንድ ምርጥ እቃ አድርጌሃለሁ” ሲል ለስብከተ ወንጌል ጠራው እሱም እንዲህ ላለው ቅዱስ ተግባር ሲጠራ የሠላሳ ሁለት ዓመት ጎልማሳ ነበር ።

ሁለቱም ሐዋርያት በኃጢአት ጨለም የነበረውን ዓለም የወንጌልን ብርሃን ለማብራት እየተዘዋወሩ ያስተምሩ ጀመር። ቢታሰሩም ቢገረፉም የክርስቶስን ስም በአደባባይ ለመመስከር የሚያግዳቸው ኃይል አልተገኘም በሚያስተምሩበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱበትም መንገድ በመሆኑ የአራዊት ምግብ እንኳን ቢሆኑ የማይፈሩ መሆናቸውን በተቀዋሚዎቻቸው ፊት ይመስክሩ ነበር ። ጴጥሮስና ጳውሎስ የዚህን ዓለም ከንቱነት ስለሚያውቁ የእግዚአብሔርን ...ልውና የተረዱ ስለእግዚአብሔር መንግሥት ከመመስከር ቅዱስ ቃሉንም ከማስተማር ያረፉበት ጊዜ አልነበረም ።

ጠንክረውም በማስተማራቸው የክርስትና እምነት እንዲስፋፋ ወንጌልም ለሁሉ እንዲዳረስ ፤ ምእመናንም እንዲበዙ አደረጉ ። ኔሮን ቄሳርም ከቁጥጥሩ ውጭ ሆነው ስላስቸገሩት ቅዱስ ጴጥሮስ በሰማንያ ስድስት ዓመቱ በስቅላት እንዲሞት ቅዱስ ጳውሎስም በሰባ አራት ዓመቱ በሰይፍ ተመቶ እንዲሞት ፈረደባቸው እነዚህ ሁለቱ ሐዋርያት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ61 ዓ.ም. ሐምሌ 5 ቀን በፍርዱ መሰረት በሰማትነት አረፉ ።



ምርጥ ዕቃ የተባለው ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ

በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ከፈጸሙት ተግባርና ካሳዩት የወንጌል እንቅስቃሴ ይልቅ ከሞቱ በኋላ በተደረገው እንቅስቃሴ ብዙ ተከታዮችን ሊያስነሳ ችሎአል። ለምሳሌ የወይን ዛፍ በቆረጡት መጠን ለባለቤቱ ብዙ ፍሬ እንደሚያበረክት ሁሉ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስም በሞታቸው ብዙ ምዕመናን ለቤተ ክርስቲያን ሊያፈሩ ችለዋል ኔሮን ቄሳር ግን ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ጳውሎስን በሞት የቀጣቸው የቤተ ክርስቲያንን እርምጃ ወደኋላ ለመጎተት ነበር ቤተ ክርስቲያን ግን እርምጃዋን ወደፊት ከማስፋፋት በቀር ወደኋላ ባለማስትዋ አላማው ሳይሳካለት ቀረ ።

ስለዚህ የቅዱስ ጳውሎስና የቅዱስ ጴጥሮስ የሕይወት ታሪክ በክርስቲያን ዓለም ውስጥ እንደ አጥቢያ ኮከብ ሲያበራ ይኖራል ክርስቲያኖችም እነሱ የሠሩትን ተግባርና የጻፉትን መልእክት እያነበቡ ከክፉ ተግባራቸው ወደ ንስሐ እንዲመለሱ ስለሚስባቸው የሕይወት ታሪካቸውን ሕያው አድርጎት ይኖራል።

ይህ ከሆነ የመኖርም የመሞትም ጥቅሙ ም ሆነ ጉዳቱ የሚታወቀው ከሞት በኋላ ለሌሎች እንደዚህ ባለው ተግባር ሲገለጽ ነው ። ወይም ታሪክ ሆኖ ለሌላው ጥሩ ትምህርትና መልካም ምሳሌ ሆኖ ሲኖር ነው ። ስለዚህ ነው ሐዋርያው “በሕይወት ብኖር ፤ ብሞትም ክርስቶስ በሥጋዬ ይከበራል ያለው ፊልጵስዩስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 21 አባባሉ መልካም ነው የሥራ ታሪክ የሌላቸውን ሲወቅስ የሥራ ታሪክ ያላቸውን ደግሞ ያሞግሳልና

ይህንንም ለማወቅ ብንፈልግ ወደዚህ ዓለም ብዙ ሰዎች መጥተዋል እያሌ ዘመናትም ኖረዋል ለሕዝብ ጥቅም ሠርተው ያለፉት ግን ጥቂቶች ናቸው እንዲህ ያሉትም ሰዎች እንኳንስ ከሞት በኋላ የሕይወት ታሪክ ሊኖራቸው ይቅርና በሕይወትም ሳሉ ለራሳቸው የኖሩ በመሆናቸው በከርሠ መቃብር ተውጠው ያለ ታሪክ ቀርተዋል ማለት ነው።

ሰዎች ግን የተፈጠሩት ለሥራ ፤ ለአገልግሎት እንጂ ለመኖር ብቻ ስለአይደለ ኑሮአቸውን በሥራ ሥራቸውንም በኑሮ ማስመስከር አለባቸው ፤ “ ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል እንጂ ተብሎ ተጽፏልና” ለራሳቸው ሳ

ወደ ፲፩ ኛው ገጽ ዞሮአል



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፣ ለችግራቸው መፍትሔ የ ..ሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።



አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቍጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ

ለትንሣኤ መጽሔት ምን እንርዳዎ
ዓምድ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላምታዬን አቀርባለሁ ፡ በቁጥር 42 ትንሣኤ መጽሔት ላይ ዲያቆን ጥላሁን ገብሬ በጻፈው ጥያቄ መ ይምይማያ ላይ የማይሠራ አይብላ የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል በመጥቀሱ እጅግ ደስ ብሎኛል ።

1ኛ በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 42 ምን እንርዳዎ በሚል ርዕስ የተጻፈውን ሳነብ ስለሥጋ ወደሙ ያልገባኝ ነገር አለና ስለዚሁ ልጠይቅ እወዳለሁ "ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ፡ ወይኑ ተለውጦ ደመ አምላክ ይሆናል ይኸውም ነፍስ የተለየችው ፣ መለኮት የተዋሀደው ነው ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ሰፋ ያለ መግለጫ እጠባበቃለሁ ።

2ኛ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሥጋ ወደሙ መለወጥ የምታምን ከሆነ በሥጋ ወደሙ ምክንያት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለው ልዩነት ምን እንደሆነ እንዲብራራልኝ በትህትና እጠይቃለሁ ።

ተማሪ ኒኮላ ኪሞን
ደብረ ሰላም ት ቤት
ጐንደር

ተማሪ ኒኮላ ኪሞን የላክህልንን ጥያቄ ተመልክተነዋል ። 1ኛ በቁጥር 42 ላይ ዲያቆን ጥላሁን ገብሬ የማይሠራ አይብላ የሚለውን ቃል በመጥቀሱ ያለህን አድናቆት ገልጠሀል ። ዲያቆን ጥላሁን ጠቀሰው ያልከውን ቃል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያስተማረው ለከፍተኛ ቱም ነገርና ለዘላቂታም መፍትሔ ጭምር ነው ።

ይኸውም ሐዋርያት ያስተምሩ በነበረበት ወቅት ሥራ ፈቶች እጅግ ከመብዛታቸው የተነሣ ሠራተኛውን ሕዝብ አላሠራ ከማለታቸውም በላይ በነገር ሥራ ፣ በስድብ በማሽሟጠጥ ፣ በአጠቃላይ ተገቢ ባልሆነ ተግባር እየተገቡ እነርሱ ያላስተማሩትን ቀጥተኛ ትምህርት እያጣመሙ ያስተማሩት ስለነበረ ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ ዓይነቱን ትውልድ በሚከተለው ቃል ገስፆታል ። "ወንድሞች ሆይ ከእኛ እንደተቀበለው ሳይሆን ያለሥርዓት ከሚሄደው ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን ። እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና ። በእናንተ ዘንድ ያለሥርዓት አልሄድንምና ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራ እንዲያው አልበላንም ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ ያልሥልጣን ስለሆንን አይደለም። ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና ሥራ ከቶ ሳይሠሩ በሰው ነገር እየገቡ ያለሥርዓት ከእናንተ ዘንድስለሚሄዱ ስለአንዳንዶች ሰምተናልና ። እንደነዚህ ያሉትንም በፀጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን ። እንመክራቸውማለን ። እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ" 2ኛ ተሰ 3 ፥ 8 - 13 ሲል ለሥራ ፈቶች ለነገረኞች ለአታላዮች ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥቶአቸዋል ። ዛሬም በዚህ ዓይነት የጥፋት መንገድ እየተጓዙ ብዙ መሰናክል የሚፈጥሩና ሌላው የደከመበትንም ለመብላት የሚንገላወዱ ነገረ ሰራዎች አታላዮች እየበዙ በሄዱበት ጊዜ የማይሠራ አይብላ የሚለው ጥቅስ ወቅታዊ በመሆኑ ዲያቆን ጥላሁን ገብሬ በተፈለገው ጊዜ ጠቅሶታል ።

2ኛ ስለሥጋ ወደሙ የቀረበው ጥያቄ ነው ። ምስጢረ ቁርባንን ለመመርመር የምንችለው በመንፈስ እንጂ በሥጋዊ አስተሳሰብ ባለመሆኑ ጥንቃቄ ሊኖረን ይገባል ። አንተ የጠየቅኸው እንኳ "ነፍስ የተለየችው መለኮት የተዋሀደው" ስንል በዓይነ ሥጋ እያየነው በእደ ሥጋም እየዳሰስነው በአምሳለ ኅብስትና ወይን እየታየ አይደለም ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሥልጣን በሰጠው ካህን ጸሎት በእግዚአብሔር ሥልጣን ተለውጦ ሥጋ አምላክና ደመ አምላክ እንደሚሆን ማመን ነው መለኮት የተዋሀደው ነፍስ የተለየችው ስንልም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ" አባ አመኃፅን ነፍስየ ውስተ እዴከ" በማለት በራሱ ሥልጣን ነፍሱን ከሥጋው ለየ መለኮት ግን በሁሉ ምሉዕስለሆነ ከነፍስ ጋር ወደ ሲኦል ወርዶ በሲኦል ለነበሩ ነፍሳት ነፃነትን ሰበከ ፣ ነፃም አወጣቸው ወዲህም መለኮት በሥጋ በመቃብር አደረ ታዲያ የምንቀበለው ሥጋ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተዋሀደው ነው ። ክርስቶስ የተወሀደውም ሥጋን ብቻ ሳይሆን ነፍስንም ጭምር ነው ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዕለተ አርብ በዘጠኝ ሰዓት ስለእኛ ሕይወት ነፍሱን በገዛ ሥልጣኑ ከሥጋው ለየ ። መለኮት ግን ከሥጋም ሆነ ከነፍስ አል ተለየም ።

እኛ የምንቀበለውም ይኸው በዕለተ ዓርብ የተሰቀለውና መለኮት ያልተለየው አምላኳካዊ ሥጋ ነው ። ዳሩ ግን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋ ነፍስ በተለየችው ጊዜ እንደ እሩቅ ብእሲ ፍጹም በድን አይደለም ።

መለኮት የተዋሀደውና ሕይወትነት ያለው ለሌሎችም ፍጹም ሕይወትን የሚሰጥ በመሆኑ ሙቀትነት ያልተለየው ነው ። ስለሥጋ ወደሙ ከተወያየን ዘንድ ስለ ምሥጢረ ቁርባንም በመጠኑ እንነጋገር ። "ምሥጢረ ቁርባን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ የምንሆንበት የእርሱን ሕይወት ተዋህደን አዲስ ፍጥረት የምንሆንበት ፣ የክርስቶስን ሕማሙን ሞቱን ማለትም ለእኛ ሲል የተቀበለውን መከራ መስቀል የምናስብበት አዲስ ሥርዓት ነው ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንኑ አዲስ ሥርዓት ሲመሠርት ለደቀ መዛሙርቱ በምሴተ ሐሙስ ኅብስቱን አንስቶ ባርኮ ንሱ ብሉ ፣ ይህ ሥጋዩ ነው" አለ ፅዋውንም አንስቶ ካመሰገነ በኋላ ሲሰጣቸው ሁላችሁ ከዚህ ጠጡ ፣ ይህም ለብዙዎች የኃጢአት ማስተሰረያ ይቅርታ ማግኛ ይሆን ዘንድ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው በማለት ሥጋውና ደሙ የዘለዓለም ሕይወት መሆኑን ያረጋገጠው ።

ከዚህም ጋር የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም ፣ በእኔ የሚያምንም ከቶ አይጠማም ዮሐ. 6 ፥ 51

ኅብስቱና ወይኑ እንዴት እንደሚለወጥ ለመረዳት ካስፈለገ የምናቀርበው ኅብስትና ወይን በእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድና በቃሉም በካህኑ ጸሎት ተለውጦ ሥጋ አምላክ ፣ ደመ አምላክ ይሆናል ብለን እናምናለን ፣ ይህም ይታወቅ ዘንድ ይህ ኅብስት ሥጋዩ ነው ፡ ይህም ወይን ደሜ ነው ሲል የተናገረውን መለኮታዊ ቃሉ አረጋግጦልናል 3ኛ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት በሥጋ ወደሙ ያለው ልዩነት እንዲብራራልኝ ለምትለው ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ስትል የትኛውና የትኛዋ እንደሆኑ ግልጽ አልሆነልንም ቢሆንም በግምት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን ይመስለኛል ።

ስለዚህ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለው የነገረ መለኮት ልዩነት በዚህ ዓምድ መገለጽ አይችልምና የሁለቱን አነስተኛ መለያየት ለመረዳት በአካባቢህ ያሉትን ሊቃውንት መጠየቁ ይበቃል ።



---

# ከሞት በኋላ ....

ከ ፀኛ ገጽ የዞረ

ይሆን ለሕዝብ የኖሩ ጥቂት የዕውቀት ጀግኖች እንዳሉ እስቲ እንመርምር እነሱም እነሶቅራጥስ ፣ የታሪክ አባት የተባለው ሄሮዶቱስ በጠቅላላው ጥንታውያን የግሪክ ፈላስፎች ናቸው ።

እነዚህም በሕይወተ ሥጋ ሳሉ አገራቸውንና ሕዝባቸውን በእውቀት በጥበብ አበልጽገው ፣ በምክራቸው ፣ በዘዴአቸው በትምህርታቸው ወገናቸውን አክብረዋል ከሞቱም በኋላ በየጊዜው ከሚነሳው ትውልድ ጋር አብረው እየተነሱ ዓለምን በሥራቸው ያከብሩታል በሕይወተ ሥጋ ካሉት መምህራንም ጋር አስተማሪእየሆኑበየዩኒቨርስቲው ሲያስተምሩ ይኖራሉ በእውቀታቸውና በጥበባቸው የዓለምን መንፈስ ሲያበለጽጉና ሲያድሱ ይኖራሉ ።

እነዚህ ብቻ አይደሉም ማእከል ሚካኤል ፋራደይ የተባለው ሊቅም ዲናሞ የተባለውን የኤሌክትሪክ መብራት ሲፈለስፍ ቶማስ ኤድሰን የተባለ ሊቅ ደግሞ ብርሃን የሚሰጠውን አምፑል ፈጥሮአል እነዚህ ሁለት ሊቆች በሕይወተ ሥጋ ሳሉ በጨለማ ለሚኖረው ሕዝብ በሥራቸው ታላቅ ብርሃንአብርተውለታል ከሞቱም በኋላ በእውቀታቸውና በሥራቸው ዓለምን ሲጠቅሙ ይኖራሉ ።

ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስም በሕይወተ ሥጋ ሳሉ በእውቀታቸው በትምህርታቸውና በምክራቸው የመንፈስ ብልጽግናን ለዓለም አበርክተዋል ጨለማ የሆነውንም ዓለም በትምህርታቸው አብርተውታል ከሞቱም በኋላ በየዘመኑ ከሚሾሙት ጳጳሳትና መምህራን ጋር በመሆን በየቤተ ክርስቲያኑ በመንፈስ እየተገኙ ምእመናንን ሲያስተምሩ ይኖራሉ በጻፉትም መልዕክት የሰውን ልጅ ሲመክሩና የመንፈስ ብልጽግናን ሲሰጡ ይኖራሉ ።

እንግዲህ ለሀገርም ሆነ ለወገን እንዲሁም ለቤተ ክርሳቲያን የሥራ ሰዎች የሰጡትን በረከት ተመልክተናል በሰሩትም ሥራ ከሞት በኋላ የሕይወት ታሪካቸው ሕያው ሆኖ እንደሚኖር ተገንዝበናል እኛም ወደዚህ ዓለም የመጣነው ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን እየሰራን፣ሌላውም እንዲሰራ እያደረግን የእግዚአብሔርን ቸርነት ለሌላው እንድናስተላልፍ ነው በሥራችንም ፣ በእውቀታችንም እኛ ብቻ እንድንበለጽግ ሳይሆን ሌላውንም የሀብትና የመንፈስ ባለ ጸጋ እንዲሆን መምከር ይገባናል ከሞት በኋላ የሕይወት ታሪክ የሚገኘው በዚህ መንገድ ነው ይኸውም ካልሠራንበት የጥፋት ፣ ከሠራንበት ግን የመዳን ምልክት

ነውና ።

አለቃ ነብየ ልዑል ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## የ ቅዱሳት አንስት ቅዱስ አገልግሎት

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ ኢየሩሳሌምና በገሊላ አውራጃ በልዩ ልዩ ቦታዎች እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ጊዜ ብዙ ሕዝብ ፤ ሴቶችም ወንዶችም እርሱን እየተከተሉ ትምህርቱን በሚገባ እየተከታተሉ በጥያቄውና በመልሱም ይረኩ እንደነበረ በቅ መጻሕፍት ተጽፎ እናገኛለን ። በጌታችን የተመሰረተችዋን ቤተክርስቲያን ያጸኑ የመጀመሪያዎቹ መቶ ሃያ ቤተሰብ ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ ሰላሳ ስድስት ቅዱሳት አንስት ይገኙባቸዋል ። 36 ቱ ቅ አንስት የጌታን ትምህርት መከታተል ብቻ ሣይሆን በጊዜው ተገኝተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አገልግለውታል ፡ ከእነዚህም መካከል በገሊላ ባሕር በስተምዕራብ በኩል መግደላ ከሚባለው መንደር የነበረች ወይም በቦታው ስም ማርያም መግደላዊት እየተባለች የምትጠራዋ ማርያምና ዮሐና ፣ ሶስና እንደዚሁም ሌሎች ብዙ ሴቶች ጌታን በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር ።ሉቃ 8 ፣2 ፣ 10 ፣ 38-42 ፣ ዮሐ. 12 ፣ 1-2 ፡ የ 36ቱ ቅ አንስት የእምነት ጥንካሬ ለሌሎችም መሠረት ነው ፣

ቅድስት ድንግል እመቤታችን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና በድንግልና ወንድ ልጅን ትወልጃለሽ በአላት ጊዜ እንደ ዘካርያስ ሳትጠራጠር ሉቃ 1፣5-20 ፡ እንዳልከኝ ይሁንልኝ ሉቃ.1 ፣ 37-38 ስለአለችው በእግዚአብሔር በማይመረመር ጥበቡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ለመውለድ በቅታለች። ማርያም መግደላዊትም በእምነት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ ባወቀች ጊዜ ከመቃብሩ ትንሣኤውን ለደቀ መዛሙርቱ ሰብካለች የትንሣኤውንም ምስጢር ለማየት ከሌሎች ሁሉ ቅድሚያ ያላት ፣ ጥርጣሬን ከልቧ ያስወገደች ከ36ቱ ቅ አንስት አንዷ ናት ። ሌሎች ደቀ መዛሙርት ግን የ ባቸውን ድንዳኔ አይቶ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደነ ፋቸው ከቅ መጽሐፍ እንረዳለን ። ማር. 16 ፣ 9-14 ፡ ማርያም እንተ እፍረት ወይም ዋጋው እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሽቱ የቀባቸው ማርያም በሠራችው ኃጢአት ከልብ ንስሐ በመግባትና ገና ገጹን እንኳ ሳታይ ኃጢአትን የማያስተሠርይ መምህር መጥቶአል ማለትን በሰማች ጊዜ የከበረ ሽቱ ገዝታ ጌታ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀምጦ ወደነበረበት ወደ ለምጻሙ ስምዖን ቤት ገብታ በእንባዋና በሽቱ ስለአጠበችው ከእምነቷ ጽናት የተነሣ ኃጢአትሽ ሁሉ ተሠርዮልሻል ብሎአታል ።

ያገኘችው ጸጋ ይህ ብቻ ሳይሆን አብረው ከነበሩት ከ120 ቤተሰቦች መካከል ለአንዱ እንኳ ያልተሰጠው ወንጌል በተሰበከበት ሁሉ እርሷ ያደረገችው ለእርሷ መታሰቢያ እንዲሆን ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ቃል ከሁሉም ይልቅ ብልጫ ያለው ነው ማቴ 26፣ 6 ፣ ማር 14 ፣ 3 ሉቃ7 ፣ 36 - 38 ዮሐ12፣ 1- 8 ፣

ይልቁንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ጊዜ ትምህርቱን ለመስማት ሆነ ገጹን ለማየት ሕዝብ በሕዝብ ላይ እየተነባበረ ከፊቱ ለመቅረብ ያልቻለች ብቻ ልብሱን ብነካው ከበሽታዬ እፈወሳለሁ ስትል 12 ዓመታት ሙሉ በማያቋርጥ የደም ምታት ትሰቃይ የነበረችዋ ሴት የእምነትዋ ጥንካሬ ወይም ጽናት ፈውስን እንዳስገኘላት ማር5፣25-34እና ሁለተኛዋም ግሪካዊት ሴት በልጅዋ ለይ ያለው ርኩስ መንፈስ በጌታ ኃይል እንዲለቅ ክርስቶስን በለመነች ጊዜ ልጆቹ በፊት ይጠግቡ ዘንድ ተዪ ፣ የልጆችን እንጀራ ለቡችሎች መጣል አይገባም ቢላት ጌታ ሆይ ቡችሎችም እንኳ የልጆችን ፍርፋሪ ይበላሉ ስትል ተከራከረችው የእምነቷን ጥንካሬ አይቶ ስለዚህ ቃልሽ ሂጂ ጋኔኑ ከልጅሽ ወጥቶአል ማር ፡ 7 ፡ 24 - 30 በማለት መድኃኒታችን ክርስቶስ በሴቶች ላይ ያለውን የእምነት ጥንካሬ እጅግ አድርጎ አድንቆአል ። ስለዚህ በቅድስት ድንግል እመቤታችን ይኩነኒ በከመትቤለኒ በሚለው ቃል የተመሰረተው እምነት ለሌሎች ሴቶች ሁሉ የማይናወጥ መሠረት መሆኑን ከዚህ በላይ በሁለቱ ሴቶች የተደረገውን ፈውስ ተረድተናል ። ከዚህም ሌላ ሐዋርያው ቅጳውሎስ በሚያስተምርበት ጊዜ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክቱ የጢሞቴዎስ የእምነት ጥንካሬ በጢሞቴዎስ ላይ ሊሰራ የቻለው ቀደም ሲል ሎይድ ተብላ ትጠራ በነበረችው በአያቱና በእናቱም በኤውንቄ የነበረው ጠንካራ እምነት በእርሱ ላይ ያለ ግብዝነት ያለ የልብ እምነት ከነርሱ መሆኑን በ2ኛ ጢሞ 1 ፣ 5 ላይ ስለገለጸው የ 36ቱ ቅ/ አንስት የእምነት ጥንካሬ ለሌሎችም መሠረት መሆኑን በ ሚገባ ለማ



ወቅ ይቻላል ።

ስለ ቅ አንስት ክብርም ቅ ያሬድ በ ዜማ መጽሐፉ በድጓ መዝሙር ደርሶላቸዋል ። በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መታሰቢያቸውን የዳግም ትንሣኤ ዋዜማ ቅዳሜ ታከብራ ራለች ።

በሰማዕትነት ያረፉና በብህትውናም የነበሩ ቅ አንስት ብዙዎች ናቸው

ስለክርስትና እምነት መስፋፋት ሰይጣናዊ ቅናት ይዞአቸው በነበሩ በዲዮቅልጥያኖስና መክስምያኖስ ከሃድያን ነገሥታት ትእዛዝ የክርስቶስን ስም የሚጠራ ሁሉ በሰይፍ ይታረድና በእሳትም እንደ አሮጌ ጨርቅ ይቃጠል እንደነበረ የ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳናል ። በዚያም ጊዜ በሰይፍ ከተገደሉ ብዙ ሴቶች አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ይቻላል ። ለምሳሌ ሶፍያ የምትባለዋ ንግሥት እስከልጆቿ ክሮስቶስን ስታመልክ በመገኘትዋ ምክንያት ክርስቶስን እንድትክድ ብትጠየቅ ፈቃደኛ ባለመሆንዋ ከልጆችዋ ጋር በሰይፍ ታርዳለች ፣ ሶፍያ ንግሥትም የዓለም ክብርና በዓለም ላይ ንግሥት ተብሎ መኖር ሳያታልላት ለማያልፈው ዓለም ስትል ከደናግል ልጆችዋ ጋር በሰማዕትነት ዓርፋለች ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም መታሰቢያዋን ነሐሴ 3 ቀን ታከብራለች ፣ ቅ ያሬድም ስለ ሃይማኖቷ ጽናትና ከልጆቿ ጋር በሰማዕትነት እንዴት እንዳረፈች ድጓ እየተባለ በሚጠራው የዜማ መጽሐፍ ላይ በሚገባ በሰፊው ጽፎላታል ።ጺላግያ፡- የአንፆኪያዋ ጺላጊያም ከቤተሰቦቿ ጋር በቤት ውስጥ እንዳለች ያሉበት ቤት በወታደሮች እንደተከበበ ባየች ጊዜ ክብረ ንጽሕናዬ እንደተጠበቀ ነፍሴን ለፈጣሪዬ አሳልፌ እሰጣለሁ በማለት ገና የ15 ዓመት ለጋ ወጣት ሳለች ከመስኮት ላይ ተወርውራ ከቤታቸው ጎን ከሚገኘው ባሕር ገብታ በ311 ዓ.ም. እንደሞተች የጥንት ቤተክርስቲያን ታሪክ ምሁር ጂ .ኤፍ .ራይት ይናገራል እንደዚሁም በሰም ከእርስዋ ጋር ተመሳሳይ የሆነችዋ የጠርሲስ ተወላጅ ድንግል ጺላጊያ ደብረ ዘይት እየተባለ በሚጠራው ተራራ በብሕትውና ስትኖር ሳለች የንጉሡ ወታደሮች ለንጉሡ ባለቤት እንድትሆን ቢጠይቋት አይቻለኝም ስለአለቻቸው በእሳት እንድትቃጠል አድርገዋል ።

በብሕትውና ዓለምም ሴቶች እንደነበሩ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ይቻላል ። ቅ/ማክሪና ቅድስት ማክሪና በቂሣሪያ ቀጰዶቅያ በ328ዓ.ም. ተወለደች ። ለእርሷም ዘጠኝ ወንድሞች ነበሩዋት ። ከነዚህም መካከል በጣም የታወቁት ታላቁ ቅ ባስልዮስ ፣ የኑሲሱ ቅ ጎርጎርዮስና ጴጥሮስ ናቸው ። ቅ/ማክሪና የምሥራቅ ባሕታዊት በመባል በጥንት የቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የታወቀች ናት ፣ በጥንት ዘመን [illegible] ጥቃም የብሕትውናን ገዳም ከመሠረቱት አንዷ ናት ቅ/ማክሪና ፓንቱስ በሚባለው ስፍራ የሴቶችን ገዳም የመሠረተችና ሴቶችም ከዚህ ገዳም በቤተሰብ ደረጃ በአንድነት በፍቅር እንዲኖሩ ያደረገች ታላቅ ባሕታዊት ናት ። ወደዚህ ዓለም ከመግባቷ በፊት ቀደም ሲል ወንድሞቿም ሆኑ እርሷ ከወላጆቻቸው ጋር ሳሉ ፣ ባስልዮስም በ351ዓ.ም ወደ አቴና ዩኒቨርስቲ ከመሄዱ በፊት በቤተሰብ ደረጃ ይሰጣቸው በነበረው የሃይማኖት ትምህርት በሚወዳደሩበት ጊዜ ወንድሞቿን ቅ/ባስልዮስንና ጴጥሮስን ታሸንፍ እንደነበረ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተጽፎ እናገኛለን ። ቅ/ባስልዮስም ከአቴና እንደተመለሰ የርሷን ፕላን በመከተል በፓንቱስ 2፣ 3፣ 5 ሆነው ይኖሩ የነበሩትን በአንድነት በማኅበር እንዲኖሩ ገዳምን መስርቶአል ፤ ቅ/ማክሪናም በብሕትውና ለብዙ ጊዜ ከኖረች በኋላ በ 379 ዓ.ም ራሷ በመሠረተችው ገዳም ዓርፋለች ።

ግብፃዊት ማርያም ፣ - የእስክንድርያዋ ማርያም በጥንት የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው በመጀመሪያ የነበረው የክርስትና ሕይወቷ ያልተስተካከለ እንደነበረ ቢታወቅም በኋላ ከሰው በመለየት በዮርዳኖስ አካባቢ አርባ ሰባት ዓመታት ሙሉ ብቻዋን ዘግታ ስለ ሠራችው በደል በጾምና በጸሎት ንስሐ እንደገባች ይነገራል በመጨረሻም በ421 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ልትለይ ስትል ቆዝሞስ የሚባል ቄስ ካለችበት በረሃ ድረስ ሂዶ ቅዱስ ቁርባን ከሰጣት በኋላ ወዲያው እንደሞተች ይታወቃል። የኖረችበት ዘመን ከ 344- 421 ዓ.ም ነው።

ባሕታዊት ኤልሣቤጥ ፣ የሃንጋሪዋ ባሕታዊት ኤልሣቤጥ ከንጉሥ እንድርያስ በ1207 ዓ.. ተወለደች ገና የ4 ዓመት ሕፃን ሳለች ለሉይስ 4ኛ ታጭታ ከ10 ዓመት በኋላ እጮኛዋ የ21 ዓመት ወጣት ሲሆን የጋብቻን ሥነ ሥርዓት ፈጸሙ 3 ልጆች እንደወለዱ በጦርነት ላይ ሳለ ወዲያው በአጭር ጊዜ ውስጥ ስለሞተ ባሕታዊት ኤልሣቤጥ ኑሮዋን በጸሎት ብቻ ወሰነች ። አንድ ጊዜ ከእህልና ከውሃም ተከልክላ እንደነበረ ይነገርለታል ። ከዚያም ብቸኝነትን አጥብቃ ድሆችንና የታመሙትን ብቻ በመርዳት ላይ ሳለች በ 1231 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች ።

ለክርስትና መስፋፋት ሴቶች ታላቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

በመጀመሪያው በሐዋርያት ዘመን የአብያተ ክርስቲያናት ቁጥር እጅግ በጣም አነስተኛ በነበረበት ጊዜ ክርስቲያኖች በየግለሰቦች ቤት እየተሰበሰቡ ይጸልዩ እንደነበረ እናውቃለን የመጀመሪያዋም የክርስቲያኖች የጸሎት ቤት ወይም የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም የማርቆስ እናት ከቅ/አንስት አንዷ የነበረችው የማርያም ቤት ነበር ። የሐዋ. ሥራ 12 ፣ 12 ፣ እንደ ቅ/ማርያም ቤታቸውን ለክርስትና መስፋፋት ሲሉ የጸሎት ቤት ያደረጉና መንፈሳውያን ዜናዎችን ለክርስቲኖች ያደረሱ ፣ የተሰወሩ ቅዱሳት ንዋያትን ያስገኙ ብዙ ቅዱሳት አንስት ይገኛሉ ።

እዮቴርያ ፣ የኢየሩሳሌሙ ቅ ቄርሎስ በ286 ዓ.ም. እንደ ሞተ ከ10 ዓመት በኋላ እዮቴርያ ኢየሩሳሌምን ስትጎበኝ የቅ/ቄርሎስን ቅዳሴ በማግኘቷ ተቀብሮ ሊቀር የነበረውን ድርሰቱን ወደ ሀገር ስትመለስ በጋዜጣ ላይ በማውጣት ከ

ተከታዩን በገጽ ፲፮ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፤ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፡፫) ።

## ክርስቲያናዊ ጋብቻ

የዚህ ጋብቻ መሠረቱ "ሰው አባቱንና እናቱን እንኳ እስከመተው ይደረሳል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል" ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ ሲል እግዚአብሔር አምላክ ገና በሰው ተፈጥሮ አጀማመር ላይ የተናገረው ቃል ነው ። (ዘፍጥ. 1 ፡ 2 ፡ 24) ።

ይህንም በማረጋገጥ ከሐዲስ ኪዳን ጋር በማስተባበር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ይሰብክ በነበረበት ጊዜ ጸሐፍት ፈሪሳውያን "ማንም ሰው በገጠመው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ይገባዋልን ?" ሲሉ ላቀረቡለት ጥያቄ ሲመልስ እንዲህ አለ" እግዚአብሔር ገና ሲፈጥራቸው (በመጀመሪያ) ወንድና ሴት እንዲሆኑ አደረገ ። ስለዚህም ሰው አባቱንና እናቱን እንኳ ትቶ ከሚስቱ ጋር ይተባበራል ፤ ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ ፤ … እግዚአብሔር አንድ ያደረገውንም ሰው መለየት አይችልም ። (ማቴ. 19 ፡ 3 - 4) ።

ይህም ቃል የሚያስረዳን ጋብቻ ሊከለስ ፦ ሊፈርስ ወይም ሊለዋወጥ የማይገባ ዕኑዕ (ቀዋሚ) ሕግ መሆኑን ነው ። እንዲያውም ጌታ ሲያስተምር በተራራው ስብከት ማቴ. 5 ፡ 31 - 32 በአረት አንዲት ሴት ምክንያት ከተገኘባት የተፈታችበት ሁኔታ ተገልጦ በጽሑፍ ተሰጥቶዋት እንድትፈታ ታዞ የነበረውእንኳ ያለአግባብ መሆኑን በመግለጥ "ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል ፤ የተፈታችውንም ያገባ ያመነዝራል" በማለት የመፋታት ምዕራፍ መዘጋቱን አመልክቷል ።

ሐዋርያው ጳውሎስም ጋብቻን በማስመልከት የቆሮንቶስ ሰዎች የጻፉትን ጥያቄ መሠረት በማድረግ በጻፈው መልእክት (1ኛ ቆሮ. 7 ፡ 10 - 11) "ሚስት ከባልዋ አትለይ ፤ ብትለይ እንኳ ሌላ ባል ሳታገባ ትኑር ፤ ወይም ከባልዋ ትታረቅ ፤ ባልም ሚስቱን መተው አይገባውም" በማለት ደንግጎዋል ። ወደ ሮም በጻፈውም መልእክቱ 7 ፤ 2 - 3 "ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት እስካለ ድረስ በሕግ የታሠረች ናት" ማለቱ ይታወሳል ። ወደዕብራውያን በተጻፈ መልእክቱም "ጋብቻ በሁሉ ዘንድ የከበረ ነው መኝታውም ንጹሕ ይሁን" በማለት ቅድስናውን የተናገረ ሲሆን ወደጢሞቴዎስ ለመጀመሪያ ጊዜ በጻፈው መልእክቱ (4 ፤ 2 - 4) በኋለኛው ዘመን ተነሥተው መጋባትን የሚከለክሉ የውሸት መምህራንን አውግዟል ።

ይህም ሁሉ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት የጋብቻ መፍረስ እንደ አንድ ትንሽ መንግሥት መፍረስ ያህል ስለሚቆጠር የማኅበረ ካህናትና የምዕመናንም ሥርዓት ኑሮ መልክ ማጣትና መዘበራረቅ ለአንድ አገር ዜጋ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ኅብረተሰብአዊ ኑሮ መናጋትም መጥፎ አርአያና ምሳሌ እንደሚሆን ታምኖበት ነው።የአንድ ሕዝብ ወይም መንግሥት መሠረቱ ጋብቻ ነውና መንግሥትም ራሱ የቤተሰብ ድምር ነው ።

በሌላ በኩል የምናየው ማስረጃ ባልና ሚስት በክፉም ፤ በደግም ጊዜ መፋታት ሳይኖርባቸው የሚገጥማቸውንም ፈተና ሁሉ አብረው መቋቋም እንዳለባቸው የሚያመለክቱ ዋና ዋና ድርጊቶችን ከታሪክ መማር ነው ለምሳሌ አዳምና ሔዋን በገነት 7 ዓመታት ያህል በጋብቻ ሥርዓት በተድላ በደስታ ይኖሩ ነበር ኋላም ፈተና ገጥሟቸው ከገነት ተባርረው ምድረ ፋይድ ሲወርዱ በዚህ ዓለም ኑሮ ጋብቻቸው አልፈረሰም ።ከዚያም ወዲህ የተነሡ አበው ይህኑ አርአያና ምሌ ተከትለዋል።ለማስታወስ ያህል ኖኅና ሚስቱ ሦስቱ ልጆቹና የነርሱም ሚስቶች ሳይለያዩ ተባብረው በዘመኑ ከነበረው የአሥረሽ ምቺው አመፅ ጋር ተሳትፎ እንዳይኖራቸው ራሳቸውን ጠብቀው በመገኘታቸው ወደ መርከብ ገብተው ከጥፋት ውሃ ድነዋል ። አብርሃምና ሣራ በተወለዱበት አገርና በተሰደዱባቸው አገሮች ሁሉ ደስታውንም ሆነ መከራውን አብረው ተካፍለዋል ። የሎጥ ሚስት ግን በመከራ ጊዜ በመከዳትዋ የጨው ሐውልት ሆና እንድትቀር ተፈረደባት ሌላም ማስረጃ አለ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ጸንተው እንዲኖሩ አስፈላጊ ባይሆን ኖሮ እግዚአብሔር ለአዳም ብዙ ሴቶች ሊፈጥርለት ለሔዋንም ደግሞ ከአዳም ሌላ ብዙ ወንዶች ሊፈጥርላት በቻለ ነበር ። ይህ እንዲሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ባለመሆኑ "ጋብቻ የማይፈርስና ፍችም የማይፈቀድ ነው" ተብሎ በቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ተደነገገ ።

ከዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጋብቻን በተክሊልና በቅዱስ ሥጋ ወደሙ ማሕተም ታከብረዋለች ። ከዚህ ውጭ የሚፈጸም ጋብቻ ክርስቲያናዊና ክህነታዊ መሆን አይችልም ። በአንዳንድ አጋጣሚ በተለየ ሥርዓት የሚፈጸም ወይም ባልተጠበቀ ምክንያት በሞት ወይም ከቁጥጥር በላይ በሆነ አጋጣሚ የሚፈርስ ጋብቻም እንደገና ተጠግኖ ቢገኝ በቅዱስ ሥጋ ወደሙ እስካልታደሰ ድረስ ክርስቲያናዊ ጋብቻ መሆን አይችልም ።

ስለዚህ ጋብቻን ማፍረስ ወይም መፋታት ለሕገ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለሕገ መንግሥትና ለኅብረተሰባዊ ሥርዓተ ኑሮ መናጋት ሁሉ ጠንቅ መሆኑን ልንገነዘብና ለጋብቻ መፍረስ ጠንቅ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ በማስወገድ ረገድ ብርቱ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል ።

ቄስ መከብብ አጥናው

## ሞትን የማይፈሩ

ሞትን የማይፈሩ ብዙ ጻድቃን ሰማዕታት አሉ (ነበሩ) አንገታቸውን ለሰለትዓይናቸውን ለፍላት እየሰጡ ልዩ ልዩ መከራና ሥቃይ እየተቀበሉ በሃይማኖታቸው ፀንተው በምግባራቸው ቀንተው የኖሩ ከዘመነ ብሉይ ጀምረው እስከ ዘመነ ሐዲስ ድረስ ከዚያም እስከ ዘመነ ሰማዕታት የነበሩ ጻድቃን ሰማዕታት የክርስቶስን መለኮታዊ ቃል ይዘው ሲጋደሉ ኖረዋል ። ይኸም መለኮታዊ ቃል በሥጋችሁ የሚገድሏችሁን አትፍሯቸው ነፍሳችሁን ግን መግደል አይቻላቸውምና ያለው መለኮታዊ ኃይለ ቃል እሳቱን ስለቱን እንዳይፈሩ አድርጐ አስጨከናቸው ። ከብዙዎቹም ጻድቃንና ሰማዕታት ውስጥ ኢየሉጣና ቅዱስ ቂርቆስ አሉበት ።

የእነርሱም አገራቸው ሮም ነው በ250 ዓ.ም. ገደማ የመከራ ዓውሎ ነፋስ በክርስቲያኖች ላይ ስለ ተነሣ ቅዱስ ቂርቆስ የ3 ዓመት ሕፃን ሳለ እናቱ ኢየሉጣ ይዛው ከሮም ወደ ሌላ አገር ተሰደደች የተሰደደችበትም ምክንያቱ የሮሙ አገረ ገዥ እለ እስክንድሮስ የሚባለው ፈጣሪሽን ካጂ ፤ ለጣዖት ስገጂ እያለ ስላስቸገራትና ስላስገደዳት ከሮም ተነሥታ ወደ ሌላ አውራጃ (አገር) ለመሰደድ የበቃች ስለዚህ ነው ። ጌታ ካንዱ አገር አስወጥተው ወደ አንዱ አገር ቢሰዷችሁ ወደ ሌላዪቱ አገር ሽሹ (ሂዱ) ባለው መሠረት ተሰዳ ሄዳለች ። ማቴ 10 ቁ.23 ።

ከዚያም ሳለች የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል እንደሚባለው ሁሉ ያንሸሺታው የመጣችውን አገረ ገዥ ከተሰደደችበት አገር ለጉብኝት መጥቶ አገኝችው ። ነገር ግን አንዳንድ ተንኰለኞችና እወደድ ባዮች ፤ ነገረ ሠሪዎች አይጠፉምና ሄደው ላገረ ገዡ ከሮም የመጣች አንዲት ስደተኛ ክርስቲያን ሴት ከነ ልጅዋ እዚህ አለች ብለው ነገሩባት ያም አገረ ገዥ መኰንን አስገድዳችሁ ይዛችሁ አምጧት ብሎ ወታደሮቹን እንዲያቀርቧት አዘዘ።የታዘዙትም አሽከሮች ሄደው በትእዛዙ መሠረት አስገድደው አመጧትና ከፊቱ ቆመች ። እሱም ፈጣሪዋን ክዳ ለጣዖት እንድትሰግድ ጠየቃት ። ኢየሉጣም ቂርቆስ የሚባል የ3 ዓመት ሕፃን አለኝ እውነቱን ለመረዳት ያምርህ እንደሆነ እውነቱን ከሐሰት ለይቶ ያስረዳህ ዘንድ እሱን ጠይቀው ከእግዚአብሔር ይልቅ ለጣዖት መስገድ ይገባም አይገባም እንደሆነ ይነግርሃል እሱን ጠይቀህ ተረዳ አለችው ። የታዘዙ ወታደሮች ሄደው ከቤት አግኝተው አደባባይ ይዘውት መጡ፤ ያን ጊዜ እናትና ልጁ የተቀመጡ በኪራይ ቤት ነበርና ፤ ቂርቆስም መጥቶ ከገዥው ፊት ቀርቦ ቆመ ፤ አገረ ገዥውም አንተ ልጅ ፤ ፈጣሪህን ካድ ለጣዖት ስገድ ነገር ግን እምቢ ያልህ እንደሆነ አይቀጡ ቅጣት እቀጣሃለሁ አለው (ብሎ) አስፈራራው ።

ቂርቆስም ፈጣሪዩን አልክድም ለጣዖት አልሰግድም ብሎ ስለ መለሰለት ፡ ንጉሡ ኢየሉጣንና ቂርቆስን በጅራፍ ግረፉአቸው በሽመል ደብድቧቸው ብሎ አዘዘ።የታዘዙም ወታደሮች ገረፏቸው ደበደቧቸው ብዙ ልዩ ልዩ ሥቃይ አፀኑባቸው ። ጌታም ወዲያውኑ ተገርፈው እንዳልተገረፉ ተደብድበው እንዳልተደበደቡ አደረጋቸው ። ከዚህ በኋላ ይኸን ሁሉ በእነሱ የተደረገውን ልዩ ልዩ የተአምራት ሥራ አይተው ብዙ አረማውያን በክርስቶስ አምነው ተጠመቁ ሰማዕታትም ሆኑ ለክርስቶስ መስክረው በሃይማኖታቸው ጸንተው በአረማውያን እጅ በጭካኔ ተደብድበውና ተሠቃይተው ሞቱ ። የሐምሌ ገብርኤል ቂርቆስና ኢየሉጣ ምን ያደረጉበት ነው ? የሚል ጥያቄ ቢቀርብ፤መልሱ ጣዖት አምላኪዎች አረማውያን እሳት አንድደው እንደሠለስቱ ደቂቅ በእሳት ውስጥ ስለጣሏቸው ፈጥኖ ደራሹ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ከሰማይ ወርዶ እሳቱን እንደ ውሀ ስላቀዘቀዘላቸው ነው።ከመከራውም ጽናትና ብዛት የተነሣ እናቱ ኢየሉጣ መከራውን ተሠቅቃና ፈርታ የእሳቱን ነበልባል አይታ ሃይማኖቷን ለመካድ ቀርባ ሳለች ቂርቆስ እናቴ አይዞሽ አትፍሪ ጠንክሪ ይህ ምድራዊው እሳት ምን ይጐዳን ብለሽ ነው ፤ መፍራትስ ሰማያዊውን እሳት ነው እንጅ ብሎ ወደ ፈጣሪው ወደ እግዚአብሔር እናቱን ያጽናለት ዘንድ ለመነ ። (ጸለየ) ጌታም የለመኑትን አይነሣ የነገሩትን አይረሣ ነውና ልቡናዋን አፅንቶ መከራውን ያለፍርሃት እንድትቀበል አድርጐ በሃይማኖት አጸናት ። ኢየሉጣም ልጅዋን እንዲህ ብላ አመሰገነችው ስንክሣሩም ገድሉም እንደሚለው (እንደሚናገረው) ልጄ ሆይ ከእንግዲህ ወዲህ አንተ አባቴ ነህ ፤ እኔ ልጅህ ነኝ አንተ እንደ ወላጅ አባት መከረኸኛልና እኔም እንደ ልጅ ተመክሬአለሁና አንተን የወለድሁባት ያች ሰዓትና ቀን የተባረከችና የተመሰገነች ናት ብላ ከልቧ መረቀችው ። ከዚህም በኋላ የሕፃኑን ቂርቆስ ራስ ያለ ውሃ በደረቁ ከነቁርበቱ እየገፈፋችሁ ላጩት ብሎ አዘዘና በዚያውም ላይ እሳት ውስጥ ጨምሩት አለ ። አሁንም ቅ. ገብርኤል መጥቶ ከእሳቱ ዳግመኛ ነጥቆ አወጣው ። 3ተኛም እንደ ቅ. ጊዮርጊስ መንገን ከሚባለው ከማያስጨንቅና ሰውነትን ከሚበጣጥሰው መንኰራኵር እንዲያስገቡትና ተጨንቆ እንዲሞት አዘዘ ። ከዚህም ሥቃይና መከራ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል 3ተኛ ጊዜ መጥቶ አዳነው ከእሳቱ ውስጥ አወጣው ። ስለዚህ ሐምሌ 19 ቀን ቅዱስ ገብርኤል ቂርቆስን ከነእናቱ ከእሳት ያወጣበትና ከመከራ የታደገበት ቀን ስለሆነ ቂርቆስ የሚከብረበትና የ ሚነግሥበት ስለዚህ ነው ። የ3 ዓመት ሕፃን ነፍስ አውቆ በፈጣሪው ስም መስክሮ በሰማዕትነት እንደሞተና መከራ እንደ ተቀበለ አንብበን አውቀን ተረድተናል እኛ ለእግዚአብሔር የዋልነው ውለታ የሠራነው ሥራ ምንድን ነው ፤ እንዲያውዝም ብለን በስም ክርስቲያን ነን ከማለት በቀር የዋልነው ውለታ የሠራነው ሥራ የለም ። አሁንም እኛ በተቻለ መጠን ያልተማሩትን ለማስተማር በእግዚአብሔር ያላመኑትን በማሳመን የሥራ ሰማዕት እን ሁን ይህንን ካደረግንና ከሠራን እንደ እነሱ የክብር አክሊል እንቀዳጃለን ራእየ ዮሐ. 3 ቁ. 11 እነሆ ቶሎ ብዩ እመጣለሁ ማንም አክሊልህን እንዳይ ወስድብህ ያለህን አፅንተህ ያዝ ተብሏልና ።

አባ ቸርነት ጋሻው በ





www.ethiopianorthodox.org

# ኅብረተሰብእና ባህል

## ሥራ

ባለፈው ጽሑፋችን ኅብረተሰብእና ባህል ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አንዳንድ መረጃዎችን በማቅረብ አብራርተን ነበር ። ባህል በውስጡ የሚያቅፋቸውን ዘርፎች ስንመራመር ደግሞ አእምሮታዊ ወይም መንፈሳዊና ተግባራዊ ባህል ተብሎ በሁለት ዐበይት ክፍሎች እንደ ሚመደብ ጠቅሰን በመንፈሳዊው ረገድ ባህል ኪነጥበባትን ማለትም ሥነ ጽሑፍን ፣ ሙዚቃን ሥዕልን ፣ ተግባራዊው ባህል ደግሞ በሰው ልጅ የጉልበት ጥረት ጭምር የሚሠሩ ልዩ ልዩ እደጥበባትን እንደሚያጠቃልል ገልጸናል እንግዲህ እነዚህ ሁለት የባህል ዘርፎች እንደየአፈጻጸማቸው ዘዴና ብልሃት በሥራ አማካይነት አምረውና ደምቀው ይቀርባሉ፡

ይሁንና ለብዙ ዘመናት የሰው ልጅ ባህል ሆኖ የቆየውና ሰው ከእንስሳት ልቆ የታየበት ታሪኩና ሥራው የሰፋና የጠለቀ ነው ይህንም በመጠኑ እንደሚከተለው እንመለከታዋለን ፤

በቅዱስ መጽሐፍ በአራት ዘፍጥረት የተጻፈውን ቃል መሠረት አድርገን ብንነሣ የሰው ልጅ ጥሮና ግሮ ምግቡንና ልብሱን እንዲያገኝ ታዟል ። ከዚያም መጠለያውን መሥራት አድኖ መብላት ከፊት ለፊት የተንጣለለውን ሜዳ እያረሰ የሚጠቀምበትን ዘዴ ማውጣት ማውረድ ነበረበት ። ይህንንም ለማድረግ ጊዜ እንደወሰደበት አይጠረጠርም ። ኑሮ ራሱ አንድ ሌላ ታላቅ የትምህርት መስክ ስለሆነ አስቀድሞ የእርሻውን ተግባር በከንዶቹና በመውጊያ መሣሪያዎቹ እየተረዳ መቆፈርን ቆፍሮም የሚዘራውን ፍሬ መሰብሰብን ማወቅ ነበረበት ። እንደዚሁም አርዶ የሚበላቸውን ጠምዶ የሚያርስባቸውን እንስሳት መርጦ ማስለመድ ወይም የቤት እንስሳት እንዲሆኑ ማድረግ ሌላው ግዴታው ሆነ እንዲህ እያለ ኑሮውን ለማሟላት በሚያደርገው ውጣ ውረድ ከቤተሰቡ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም ሰዎች ጋር ተቀላቅሎ በጋራ ተሰማርቶ መሥራትን ጠላቱን ወግቶ መርታትን ከዚህም በስተቀር ተሰብስቦ ስለጋራ ጉዳይ መወያየትንና ለችግሮች መፍትሄ መሻትን ተለማመደው ይህም ከእርስ በእርስ አዲስ ሀሳብና አዲስ የአሠራር ዘዴ እንዲያውቅ ረዳው ባህሉንም በዚሁ መሠረት ወደ ማዳበሩ ደረጃ ደረሰ።እርሱና ልጆቹ ለእርሻው ሥራ ሲሰማሩ ባለቤቲቱ ልጆችዋን የመንከባከብ በቤት ያለውን ምግብ የማባሰሉን ከብቶች የማገናኘቱንና የጓሮ አትክልት የመኮትኮቱን ተግባር ትካፈል ነበር። ስለሆነም እነዚህንና እነዚህን ም የመሰሉ የሥራ ዓይነቶች የኑሮ ደገፋዎች ስለነበሩ ተደጋግመው በወቅት ወይም ወቅት ሳይጠብቅ ይከናወኑ ስለነበር ከኅብረተሰቡ የኑሮ ሀልውና ጋር ሰምና ወርቅ ስለነበሩ ባህል ሆኑ ከባህልም የሥራ ባህል ተባሉ ።

የሰው ልጅ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ እንደመሆኑ መማር መመራመር የተፈጥሮ ባህርዩ ስለሆነ በተፈጥሮ በተሰጡት ሁለት እጆቹና በአንዳንድ ባልደረጃ መሣሪያዎች እየተረዳ ባደረገው መሻሻል ዛሬ ወደ ኢንዱስትሪው የሥራ ባህል ተሻግሮ ይገኛል ። ስለሆነም ጥንታዊው ሰው ዛሬ በግብፅ ምድር የሚገኘውንና በታሪካዊነቱ የታወቀው ፒራሚድ ለመሥራት ሃያ አመት የወሰደበትን የዛሬው የሥልጣኔው ዓለም ህብረተሰብእ በሥራ በፈጠራቸው የኢንዱስትሪ መገልገያዎች እየተረዳ በጥቂት ዓመታት ሠርቶ ለመፈጸም ይችላል ።

ወደ አገራችን የሥራ ባህል መለስ ስንል እደጥበቦቻችንና አንዳንድ ታሪካዊ ቅርሶቻችንን ስንመለከት በመጠኑም ቢሆን እርካታ ይሰማናል ። እዚህ ላይ ታዲያ ገበሬውን አፈር ገፊ ፣ ሸክላ ሠሪዋን ቡዳ(ጠይብ)ሸማኔውን ቁጢት በጣሽ ነጋዴውን መጫኛ ነካሽ ለሌላውም ሌላ ስያሜ እየሰጠን ባረጀና ባፈጀ ቋንቋ ባንጓደድና የባለሙያዎችን ሞራል ባንሰብር ኑሮ ገና ቀደም ብለን በኢንዱስትሪው ተሳትፎና ፈጠራ ተአምር በሠራን ነበር ።

በዚህ አጋጣሚ በቤተ ክርስቲያን የተወሰኑ ሳይሆን ከሕዝቡ ባህልና ልማድ ጋር ተያይዘው የመጡና ለሥራ እንቅፋት የሆኑ የበዓላት ብዛት ናቸው ሰው ሥጋዊም መንፈሳዊም በመሆኑ በመንፈሳዊነቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ፈጣሪው በነፍሱና በሥጋው ዘወትር ስለሚታገደው ምሥጋናውን ማቅበር ተገቢው ነው ። በሌላ በኩል በፊትህ ወዝ ብላ ስለተባለ እርሱም ቤተሰቡም ተጋግዘው ኑሮአቸውን ለማሸነፍ መሥራት አለባቸው ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን ከሥፍራ ሥፍራ ሳይለያዩ የተወሰኑ መንፈሳውያን በዓላትን በማሳወቅ ለምዕመናንዋ መመሪያናም ክር መስጠት አለባት ።እንደዚሁም ቤተ ክርስቲያን በሥራ ረገድ ያላትን ብርቱእምነት የሚያዳክምባት በቅጥር ግቢዎችዋ ውስጥ የሚታየው የልመና ልምድ ነው ። ለዚህም ከምዕመናንዋ ጋር ሆና ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ የምታገኝበትን ዘዴ ልትፈልግለት ይገባል ለልመና የሚዘረጉ ሥራፊት እጆች ለተግባር ሊዘረጉና ሠርቶአደር ሊሆኑ ይገባልና ነው ። የሥራ ባህል ለግል ለኅብረተሰብ ለአንድ አገር ሰፋም ሲል ለመላው ዓለም ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው ። በእግዚአብሔርም ፊት ቢሆን ቅን ሥራ ሞገስ ያስገኛል ስለሆነም ማንኛውም የሥራ ዓይነት ክቡር መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ለምዕመናንዋ ደጋግማ ማስተማርና ማሳወቅ ከተሰጡአት አደራዎች መሃል አንደኛው መሆኑን ታምናለች ታስተምራለችም ።

የሥራን ጠቃሚነት በአንፃሩም የስንፍናን ጎጂነት የሚገልጹ ቃላት በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ በብዙ ሥፍራዎች ተጠቅሰው ይገኛሉ ። ለምሳሌም ያህል ሰሎሞን በመጽሐፈ ምሳሌ ትጉህ ሠራተኛን በገብረጉንዳን አስመስሎ ትጉህ ሠራተኛን ገብረጉንዳን ቀለብዋን በወቅቱ እንደምታከማች ሁሉ እርሱም በወቅቱ ተግባሩን እንደሚያከናው በተጨባጭ ምሳሌ ከአስረዳ በኋላ ሰነፍ፣ግን የስንፍና እንቅልፉን ሲለጥጥ በ ዚያው ከንቱ ሆኖ በችጋር እንደሚቆራመድና እንደሚጎዳ ተናግሯል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም 12 ቱን ደቀመዛሙርቱን



ለሐዋርያዊ የሥራ ተልእኮ ባሰማራቸው ጊዜ ምዕመናን ልፋታቸውን በመገንዘብ የሚያደርጉላቸውን እርዳታ በደስታ እንዲቀበሉ በፈቀደላቸው ጊዜ «ለሠራተኛ ዋጋው ይገባዋልና » ብሏል ። እንደዚሁም ሐዋርያው ጳውሎስ ሥራ ክቡር ስለሆነ ሊደክሙለት እንደሚገባ ሲገልጽ ፣ «ያልሠራ አይብላ » በማለት ትጉህና ታታሪ ሠራተኛ የሚገባውን እንዲበላ ወይም እንዲከፈለው ሲያሳስብ በአንፃሩ ደግሞ ሰነፍ ስላልሠራ ምንም ዋጋ እንደማይታሰብለት ያስገነዝባል በዚህ መልእክቱ ቅዱስ አውግስጢኖስ የተባለ መንፈሳዊ መሪ ደግሞ እንዲያውም የሥራን ልዕልና ያልቅና « ሥራ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መስዋዕት ነው » በማለት ይህ ታላቅ መስዋዕት የጥረት ፍሬ ሆኖ እንደ አቤል መስዋዕት ለሕያው እግዚአብሔር ቢቀርብ ያለጥርጥር ተቀባይነትን እንደሚያገኝ ያስተምራል በዚህም ሰው ሁሉ ለሥራ የታጠቀ ሆኖ መሰማራት እንዳለበት ይቀሰቅሳል ።

በአጠቃላይ ሲታይ የሥራ ውጤት ታላቅ በመሆኑ የሰው ልጅ ለዘመናት ባካሄደው ጥናትና ምርምር የብስን ፣ ባህርን ፣ አየርን ፣ በእጆቹ ሥራዎች በእውቀቱ አማካይነት በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ለጥቅሙ ሊያውላቸው ችሏል ።ከደሳሳ ኅጆ ወጥቶ ማዕበል በማይነቀንቀው ሰማይ - ጠቀስ ፎቅ ውስጥ የሚኖረው በሥራው ነው ። በድንቁርናው ዘመን ዘሮቹን ይፈጅበት በነበረ የበሽታ ዓይነት ሁሉ ላይ ሥልጣንን ያገኘው በእውቀቱና በሥራው ነው ።

ቤተ ክርስቲያን የሥራን ወይም የተግባርን ቅዱስነት በማጤን"ምግባር ሥራ የሌላት ሐይማኖት ሞውት ናት » ብላ እንደማስተማርዋ ሁሉ ይህ ድንቅ ቃል በምዕመንናዋ ልቡና ተጽፎ ሀገራችንን በሥራና በጥበብ ለማሳደግ በሚደረገው ዘመቻ እስከ መጨረሻው እንደሚያበረታቸው አይጠረጠርም ።

---

### የሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት .....

ከገጽ ፲፫ የዞረ

ርስቲያኖች ሁሉ እንዲያውቁት አድርጋለች ። የቅ ቁርሎስ ን ቅዳሴም አሁን ልንገለገልበት የቻልነው በእርስዋ ጥናት የተገኘ በመሆኑ ለክርስትና መስፋፋት ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጋለች ለማለት ይቻላል ።

ዕሌኒ፡- ንግሥት ዕሌኒም በአይሁድ ምቀኝነት ለብዙ ዘመናት ተቀብሮ የነበረውን የጌታችንን መስቀል ለማግኘት ብዙ ጥረት ካደረገች በኋላ በመጨረሻም በዕጣን ጢስ ምልክትነት የተቀበረበትን ቦታ በማግኘቷ አስቆፍራ ቅ መስቀሉን ለማስወጣት ችላለች ። በዚህ ባደረገችው ታላቅ ሥራዋም ቁስጢንጢኖስንና እርሷን እንደ ሐዋርያት አድርጎ በመቁጠር መታሰቢያቸውን በተለይ ምሥራቃውያን ግንቦት 21 ቀን ሲያከብሩ ምዕራባውያን ግን ለዕሌኒ ብቻ ከፍተኛ ክብር በመስጠት መታሰቢያዋን ነሐሴ 18 ቀን ያከብራሉ ፣ ኢትዮጵያዊው ቅ/ያሬድም ቅ/ዕሌኒ ስለሠራችው ከፍተኛ መንፈሳዊ ሥራ አድናቆቱን በመግለጽ በድርሰቱ መስከረም 18 ቀን ያስታውሳታል ። ቅ/ዕሌኒ በ248 ዓ.ም. ተወለደች በ326 ዓ.ም. ደግሞ ወደ ኢየሩሳሌም የጌታን መስቀል ለመፈለግ ሄደች ። በ328 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች ። በሕይወት ስትኖርም ልጅዋ ቆስጠንጢኖስ የዙፋን ችሎት በሚያደርግበት ጊዜ አብራ እየተገኘች የታሠሩት ሁሉ ምሕረት እንዲደረግላቸው ፍርድ የጎደለባቸውም ትክክለኛ ፍትሕ እንዲታይላቸው ታደርግ እንደ ነበርና ለችግረኞችም የገንዘብ እርዳታ ትሰጥ እንደነበረ ይነገርላታል ። በተለይም በኢየሩሳሌም አብያተ ክርስቲያናትን በግል ገንዘቧ እንዳሳነፀች በሰፊው ይተረክላታል ። ይህም የሚያመለክተው ለክርስትና መስፋፋት የቱን ያህል እንደደከመችና ድካምዋም ሁሉ ፍሬአማ ውጤት ያስገኘ መሆኑን ነው ።

ማርሴሊና፡- ማርሴሊና በ325 ዓ.ም. ከንጉሣውያን ወገን በሮም ከተማ ተወልዳ ያደገችና በኋላም የጋብቻን ሥነ ሥርዓት የፈጸመች ታላቅ ክርስቲያን ናት ከባሏ ጋር ብዙ ሳይኖሩ ስለሞተባት ለሁለተኛ ጊዜ ጋብቻን ሳትፈልግ ኑሮዋን በብሕትውና ወሰነች ። እርሷም በጣም ሲበዛ ርኅሩኅት ስለነበረች ከሰዎችም ሆነ የራሷንም ገንዘብ እየሰበሰበች ለድሆች መስጠትና በጉልበቷም ድሆችን መርዳት ታላቅ ሥራዋ ነበር ። አቬንቲን ፣ ተብሎ በሚጠራው ኮረብታ ላይ የነበራትን የራስዋን ቤተ መንግሥት የክርስቲያኖች ሴቶች መሰብሰቢያ እንዲሆን አደረገች ። በተለይም ከነገሥታትና ከመሳፍንት ፣ ከሌሎች ሀብታም ወገኖችም የሆኑ ሴቶችን በመሰብሰብና በማስተማር ወደ ክርስትና ዓለም እንዲመለሱ ያደረገች ለክርስትና ዕድገት መፋጠን ታላቅ አስተዋጽኦ ያበረከተች የ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ታላቅ ባሕታዊት ናት ። የጥንት ቤተክርስቲያን የታሪክ ምሁር ድሮም የማርሴላ እንግዳ በመሆን ለ3 ዓመታት ሙሉ በርሷ ዘንድ ተቀምጦ እንደነበረ ይነገራል። እርሷም ከእርሱ ባገኘችው ምክር መጽሐፍ ቅዱስን እያጠናች ጸሎትንም እየጸለየች በምታገኘው የእርዳታ ገንዘብ ችግረኞችን ሰብስባ በመያዝ ስትረዳ ከኖረች በኋላ በ410 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች ።

ሐዋርያው ቅ ጳውሎስም በኖረበት ዘመን ብዙ ክርስቲያን ሴቶች ለወንጌል ተልዕኮ ሲሉ እጅግ አድርገው ይደክሙና እርሱንም በመልክት በኩል በሚገጥመው ችግር ይረዱት እንደነበረ አንድ በአንድ ስማቸውን እየጠራ ከሚያስታውሳቸው ክርስቲያን ሴቶች መካከል እነ ፌቤንን ፣እነማርያን ፣ እነጢርሲፃንና ሌሎችንም እናገኛለን ። ሮሜ 16 ፣ 1.2 6. 12 1ኛ ቆሮ. 9፡5፣በጠቅላላ በዘመነ ሐዲስ ስለክርስትና እምነት እድገት ታላቅ አስተዋጽኦን ስለአበረከቱ ቅ/አንስት በአጭሩ ለመግለጽ ሞከርኩ እንጂ በዘመኑ ብሉይም ቢሆን ብዙ ቅ / አንስት የእግዚአብሔርን ሕግጋት የፈጸሙና በጾምና በጸሎት ተወስነው የኖሩ ብዙዎች ናቸው ። ከእነዚህም ውስጥ በመዝሙ

ተከታዩን በገጽ ፲፰ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# ከታሪክ ማኅደር

## አባ ጎርጎርዮስ ኢትዮጵያዊ ምሑር በአውሮፓ

እኒህ ምሑር በ 16ኛው ክፍለ ዘመን ላይ የነበሩ ስመ ጥሩ ሊቅ ሲሆኑ ስማቸውና ዝናቸው ከአገር ውስጥ ይልቅ በአውሮፓ እጅግ ጎልቶ ይታያል ።

መምህር ጎርጎርዮስ ከአገራቸው ከመውጣታቸው በፊት የመጻሕፍትን ትርጓሜ በሚገባ ያጠኑ ከመሆናቸውም በላይ የአስተዳደርንና የፍርድን ጉዳይ ጠንቅቆ ለማወቅ የሚያስችላቸው የአደባባይና የፍርድ ሸንጎ የሥራ ድርሻ እንደነበራቸው ይነገራል ።

እኒህ መምህር ከአስተዋይነታቸውና ከብልህነታቸው የተነሣ በአገራቸው ውጭ ያለውን የዓለምን እንቅስቃሴ ለመመልከት ጉጉት ነበራቸውና ይኸንኑ ፍላጎት ለማርካት በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት የፖርቱጋል ጀስዊቶች ኢየሱሳውያን ጋር በመተዋወቅ ልዩ ልዩ የውጭ አገሮችን ለመጎብኘት ችለዋል ።

የካቶሊክ እምነት ተከታይ ባይሆኑም ከጀዊስቶች ጋር በመሆን ህንድን ፣ ሱዳንን ፣ ግብፅን ፣ ከዚያም ሮምን በኋላም ጀርመንን ጎብኝተዋል ።

በ1646 ዓ.ም. መምህር ጎርጎርዮስ በሮም የአቢሲኒያ ኮሌጅ በመባል በታወቀው መካነ ትምህርት ውስጥ በነበሩበት ጊዜ በሊቅነቱ የታወቀው ተማሪያቸው «ጆብ ሉዶልፍ » ሊተዋወቃቸው ችሏል፣ በዚያን ጊዜ ጆብ ሉዶልፍ ወደሮም የመጣው የኢትዮጵያ ጥናቱን ለመጀመር ነበር ።

ይህ ጀርመናዊ ምሑር አባ ጎርጎርዮስን በማግኘቱ ከአሰበውና ከገመተው በላይ ስለኢትዮጵያ መጻሕፍትና ታሪክ ሊማር በመቻሉ የሥራው ውጤት እጅግ የተሳካ ሊሆንለት በቅቷል ።

ሉዶልፍ የመምህር ጎርጎርዮስን እርዳታ ባያገኝ ኖሮ
የግዕዝ ሰዋሰው
የኢትዮጵያ ታሪክ
የአማርኛ ሰዋሰው
የግዕዝና የላቲን መዝገበ ቃላት
የተባሉት መጻሕፍት አሁን ያላቸውን ጥራትና ጥልቀት ይዘው ለመታተም ባልበቁም ነበር።

በዚህ ምክንያት አባ ጎርጎርዮስ በአሥራ ሰባተኛው ምዕት ዓመት የኢትዮጵያን ጥናትና ምርምር በአውሮፓ ለማስተዋወቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ናቸው ቢባል የአሳቡ ትክክለኛነት አያከራክርም ።

መምህር ጎርጎርዮስ ከአገራቸው ወጥተው ሮም እስኪደርሱ ይገለገሉበት የነበረው የውጭ ቋንቋ የፖርቱጋል ቋንቋ ነበር፣ በኋላ ግን ቀስ በቀስ የላቲንና የኢጣልያን ቋንቋ ለማወቅ ችለዋል ።

መምህር ጎርጎርዮስ በኤውሮፓ የተመለከቱትንና የተረዱትን ጥበብ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ለማስረዳትና ለማስተዋወቅ የነበራቸውን ከፍተኛ ፍላጎት ለማርካት ወደአገራቸው ለመመለስ ወሰኑ ።

በዚህም ምክንያት በ 1652 ዓ.ም የክረምቱ ወራት ከመግባቱ በፊት ከጀርመን ወደሮም ከተመለሱ በኋላ ከሮም በመርከብ ተሳፍረው ጉዞዋቸውን በሚዲትራንያን ባሕር ላይ ጀመሩ ፣ በጉዞውም ላይ ሳሉ ወደ ሶርያ ወደብ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው የነበሩበት መርከብ በድንገት ሃያአራት ሰዎች እንደያዘች ተገልብጣ ሰጠመች ።

በዚያ አካባቢ ይኖር በነበረው የፈረንሣይ ቆንሲል አማካይነት ም የእሳቸውና የሌሎችም ሰዎች እስከሬን ተፈልጎ ከተገኘ በኋላ እንዲቀበር ተደርጓል ።

የአሥራ ሰባተኛው ምዕት ዓመት በአውሮፓ የኢትዮጵያ ትምህርት ሊቅ የነበሩት አባ ጎርጎርዮስ በዚህ ሁኔታ ሕይታቸው ብታልፍም ትምህርታቸው እስከዛሬ የአውሮፓ ምሑራንን ሲጠቅም ቆይቷል ወደፊትም ሲጠቅም ይኖራል።

የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከብሔራዊው ትምህርትና ምርምር አልፈው በውጭው ዓለም ከፍተኛ ግምትን በማግኘት የተጠያቂነትና የመምህርነትን መድረክ ሲረከቡ ታሪክ የሊቆች ሊቆች ይላቸዋል።

የዓለምን መጻሕፍት በአማርኛ ወይም በግዕዝ ብቻ ሳይሆን በብዙዎች ቋንቋዎች ማስተያየቱ ማመሳከሩና ዕውቀትን ማደርጀቱ ለአገርም ሆነ ለውጭ አገር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል ።

የብሔራዊውንና የውጭውን ዓለም ትምህርት አጠናቅረው ለአገራቸውና ለወገኖቻቸው ለማትረፍ ብርቱ ፍላጎት የነበራቸው አባ ጎርጎርዮስ በምርምርና በትጋት የተረከቡትን መክሊት ሳያራቡ በመርከብ አደጋ ቢሞቱም ታሪካቸው እነሆ ስማቸውን ሕያው አድርጎታል ።

እንግዲህ ይኸ ዓይነቱን የሊቁን ፈለግ የሚከተሉት ሊቃውንት በናፍቆትና በተስፋ ይጠብቃሉ ።

በጥቅምት 19 ቀን 1973 ዓ.ም ቅፅ አንድ ቁጥር 1 ከተጻፈውና «ዜና ልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ » ከተባለው መጽሔት የተገኘ

### ሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት ...

ከገጽ ፲፯ የዞረ

ዘሙርዋ የታወቀች የነብዩ ሳሙኤል እናት ሐና ነቢይት፣ 1ኛ ሳሙ 11 - 10 የመጥምቁ የሐንስ እናት ቅ/ኤልሳቤጥ ሉቃ. 1 ፥ 39 - 45 ፣ የፋኑኤል ልጅ ሐና ሉቃ. 2 ፥ 36 - 38 ፣ ነቢያት ናቸው ።

ስለዚህ ቅ/አንስት ለተከታዮቻቸው ሁሉ መልካም አርአያን ስለመሠረቱ በክርስትና ዓለም ውስጥ ክርስቲያንሴቶች ከፍተኛ አገልግሎትን የሚያበረክቱና የእምነት ጥንካሬአቸውም ከር ጎራኄ ጋር ከሁሉም ብልጫ ያለው ነው

ፀሐይ ብርሃኑ







www.ethiopianorthodox.org

# የቤተሰብ ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

ረዳት እንድትሆነው ሔዋንን ለአዳም የሰጠው አምላክ የመጀመሪያ ተአምሩን ወዳጆቹና ቤተ ዘመዶቹ በሚደሰቱበት የሠርግ ግብዣ ላይ የሕዝብ አገልግሎቱን ጀመረ ። እርሱ እራሱ ያቋቋመ ሥርዓት መሆኑን በማስታወስም ጋብቻን ቀደሰ ። ወንድና ሴት በተቀደሰ ጋብቻ እንዲዋሃዱና ቤተሰብ እንዲያቋቁሙ የቤተሰብም አባሎች በሕግና ሥርዓት ጸንተው እንዲኖሩ አደረገ ።

ከዚህም ሌላ ሠርግን በእርሱና በጸድቃን መካከል ላለው ግንኙነት ምሳሌ በማድረግ «እርሱ ሙሽራው ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሙሽራይቱ ናት ስለ ሙሽራይቱ ወዳጄ ሆይ ሁሉንተናሽ ውብ ነሽ ነውርም የለብሽም መኃልየ መኃልይ 4፡7 በማለት አበብሮታል ።

እርስ በእርሳቸውም እየተዋደዱና እየተከባበሩ መኖር እንዲገባቸው አብራርቶ ማስረዳቱን ከኤፌሶን 5፡21-33 ተመለከቱ ይሉ ሥጋት የጋብቻ አንድነት ሊገኝም የሚችለው በክርስቶስ አማካይነት የተመሠረተ እንደሆነ ብቻ ነው ። በሕገ ፍቅርም ጥንካሬ ሊያገኝ የሚችለው ከመለኮታዊ ፍቅር ጋር የሆነ እንደሆነ ነው ።

የጋብቻን አንድነት ለመመሥረት የሚፈጸሙ ርምጃ ሁሉ በእውነተኛነት፣ በታማኝነትና ባለማስመሰል እግዚአብሔርን በማክበርና በመፍራትም ጭምር ሊሆንን ይገባዋል ። ጋብቻ የአሁኑንም የኋለኛውን ሕይወት የሚመለከት ነውና ነው ።

ይህንኑ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ. ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት በመከተል ሚያዝያ 25 ቀን 1973 ዓ.ም. ወ ት ቤዛዊት ቸርነትና አቶ የሽጥላ ገ ሐና በአ.አ.ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤ /ክ በሥርዓተ ተክሊልና በቅዱስ ቁርባን የጋብቻቸውን ሥርዓት ፈጽመዋል ።

ከቦታው ድረስ ተገኝተን እንደተመ ን ዘንድ እቅፍ አበባ ተበርክቶላቸው እንዳበቃ የሁለቱን በተለይም የወ ት ቤዛዊትን መንፈሳዊ አቋም የሚገልጽ ጽሑፍ በቅጽረ ቤተክርስቲያኑ ለተሰበሰቡት ምዕመናን ተነቦ በመጨረሻም



ለወ ት ቤዛዊት ቸርነትና ለአቶ የሽጥላ ሥርዓተ ተክሊል ሲፈጸምላቸው

ለክትነው ጋብቻውን በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ሲፈጽሙት ሁለት ወጣቶች የቤተ ክርስቲያኑ ካህናትና የምክህ ደናግል ማርያም የወ.መ.ማ. በመተባበር ደማቅ የሆነ አቀባበልና አሸኛኘት አድርገውላቸዋል ። በዚሁ ዕለት ለተከናወነው ሥርዓት ላይ ስለ ሁለቱ ወጣቶች የከበረ ጋብቻ መታሰቢያ እንዲሆን ከማኅበረ ካህናቱ ልዩ ልዩ መወድስን ቅኔ ቀርቦላቸዋል ። እንዲሁም ከደብሩ የወ.መ.ማ. ለሁለቱ ወጣቶች መልካም ጋብቻቸውን ማብሰሪያ ይሆ የደብሩ መንፈሳዊ ማህበር ለሙሽሮቹና ለእጀቢዎቻቸው እንዲሁም ለተጠሩት እንግዶች ያዘጋጀው ቁርስና የለስላሳ መጠጥ ግብዣ ከተፈጸመ በኋላ የቤተ ክርስቲያኑ ማህበረ ካህናት መዘምራንና የወጣት መንፈሳዊ ማህበሩ መዘምራን ደማቅ በሆነ ሥነ ሥርዓት ከአካባቢው ምዕመናን ጋር በዕልልታና በሆታ ሸኘ ተዋቸዋል ።

ተከታዩን በገጽ ፳፪ ይመልከቱ



# ይህን ያውቁ ኖርዋል ?

እጅጉ ረታ ። (ካለፈው የቀጠለ)

"እነሆ ወራት ይመጣብሻል" ብሎ ነበር ጌታ የቢታንያን ቁልቁለት ሲወርድ ኢየሩሳሌምን ባሻገር እየተመለከተ ፣ "ጠላቶሽ ይከቡሻል ፣ በየበኩሉም ያስጨንቁሻል ፣" ትንቢት ነው ። ሸሽተው ራሳቸውን ለማዳን በማይችሉ በእርጉዞች ፣ በሚያጠቡ እናቶችና በሕፃናት ፣ በሽማግሌዎችና በአሮጊቶች ላይ የሚደርሰው መከራና ሥቃይ ወለል ብሎ ስለታየው ነበር ይህን የተናገረው እንባውን እያፈሰሰ ።

ቃሉ ሊፈጸም ጥቂት ጊዜ ሲቀረው ፡ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ለነበሩ ደጋግ መምህራን የጥፋቱ ጊዜ በደጃፍ ላይ ስለሆነ - ውለው ሳያድሩ-ከተማዪቱን ለቀው እንዲወጡ በሕልም ፡ በራዕይ ይነገራቸዋል። ከተማይቱን ብቻ አይደለም እንዲለቁ የተነገራቸው ፡ ከምድረ እሥራኤል ፈጽመው ለቀው እንዲወጡ ጭምር እንጂ ። በዚያ ከሚኖሩ ምዕመናን ( ክርስቲያኖች ) አንድም ሳይቀር በሙሉ ለቀው ይወጣሉ ።

ጊዜው የፋሲካ በዓል ነው ። ወሩ ሚያዝያ-ሰባ ዓመት ከልደተ ክርስቶስ በኋላ ። ቁጥራቸው ሦስት ሚሊዮን የሚሆን አይሁድ በኢየሩሳሌም ተሰብስበዋል ። በዓሉን ለማክበር ።

በዓለ ፋሲካ ፣ ሕዝበ-እሥራኤል ከፈርዖን ቤት ባርነት የወጡበትን መታሰቢያ የሚያከብሩበት ዕለት ነው ። በሌላም አንጻር አይሁድ ከአርባ ዓመት በፊት ጌታን ለሕማም-ለሞት አሳልፈው የሰጡበት ፣ "ደሙ በእኛና በልጅ-ልጆቻችን ይድረስ ፣"ብለው ራሳቸውን በጲላጦስ አደባባይ የረገሙበት ዕለት ነው ። ታዲያ ይህን ደሙ በእኛና በልጅ-ልጆቻችን ላይ ይድረስ ብሎ ራሱን የረገመ ትውልድ የሚመትረው ጦርነት በማንዣበብ ላይ ይገኛል ። ሮማውያን የከተማዪቱን ቅጥር መፈናፈኛ አሳጥተው ከበዋታል ። ግን በቀጥታ ወጊያ ያውኑ ውጊያ ከመግጠም ይልቅ በርበሩን ይዞ ሜውጫ መሹለኪያ እንዲያጡ ማድረግን መርጠዋል ። ውሎ-አድሮ ረሃብ ጥም እንደሚፈታቸው አውቀዋልና ።

አይሁድ በከበባውም ሆነ በጦርነቱ ወቅት ይበልጥ ያጠቃቸው ፣ ይበልጥ የጐዳቸው ከሮማ ጦር ይልቅ የእርስ-በርሱ ግድያና ዝርፊያ ነው ። ቀን-ቀን ከውጭው ጦር ጋር ሲቆራቆሱ ይውላሉ ። ማታ ማታ ደግሞ ፣ "መሪ ከእኔ ወገን አወጣ ፣ ከእኔ ወገን አወጣ" ፣ በማለት በሰይፍ በጐራዴ ይተራረዳሉ ። እከሌ ወርቅ ፣ ብር ፣ ወይም የተደበቀ እህል አለው ከተባለ አበቃለት ። እንደ ኢዮብ የተወለደበትን ዕለት እስኪረግም ድረስ ያሰቃዩታል ። ለዓይን ፣ ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ልዩ ልዩ መከራና ሥቃይ ያሳዩታል ። ተሸሽቶ እንዳይመለጥ በር-በሩ ተይዟል ። ከውስጥ ደግሞ እንደዚህ ነው ። ይልቁንም በከፋ ሁናቴ እርስ በርስ ያባላቸው (ያጨካከናቸው) የረሃቡ ፣ የጥማቱና የቸነፈሩ ጉዳይ ነበር ። ከረሃቡ ጥናት የተነሳ አሪታቸው ጥንብ ርኩስ በምትለው ፣ ይፀየፉት ያነውሩት በነበረው ላይ ሁሉ- እኔ እወስድ እኔ- ተጨፋጭፈውበታል ፡ ተላልቀውበታል ። የሚላስ የሚቀመስ ነገር በመታጣቱ፣እናት የልጅዋን ሥጋ ቀቅላ እስከመብላት ደርሳለች ። ከዚህ ሁሉ መከራ የዳኑ የመሰላቸው ጠላቶቻቸውን ምሕረት ለመለመን ከቅጥሩ ውስጥ መውጣታቸው አልቀረም ነበር ። ዳሩ ግን እነሱ ክርስቶስን ያለ ርኅራኄ ጨክነው እንደሰቀሉ እነሱንም ሮማውያን በጭካኔ እየሰቀሉ እውስጥ ላሉት መቀጣጫ አርገዋቸዋል ። እውስጥ ያሉት ጐበዛዝት ምንም ሽንጣቸውን ገትረው ቢከላከሉም መቋቋም ፣ መመከት ባለመቻላቸው ሮማውያን ቅጥሩን ጥሰው ገብተው በጨበጣ ውጊያ ይህ ነው የማይባል እልቂት አድርሰውባቸዋል ።

በከፍተኛ ሥፍራ መቀመጥ የሚወዱ የካህናት አለቆቻቸውንና ሽማግሌዎቻቸውን ራቁታቸውን በአደባባይ እየገረፉ መሳቂያ መሳለቂያ አርገው ሰቅለዋቸዋል ። በዚህም በክርስቶስ ላይ የፈጸሙትን መከራና ሥቃይ ብድራት ተከፍለውታል ።

በጦርነቱ ላይ ሕይወታቸውን ያጡት አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ፣ የተማረኩ ዘጠና ሰባት ሺህ ሲሆኑ ከምርኮኞቹ ውስጥ አስራ አንድ ሺህ የሚሆኑት በረኃብ አልቀዋል ። የቀሩትም ሠላሳ -ሠላሳው በአንዳንድ ብር ተሸጠዋል ይባላል ። ብድር አይደል !

ከተማዪቱ እንዳልነበር ሆና እንድትደመሰስ ትእዛዝ ከጥጦስ ቄሣር በመውጣቱ ፍራሿን ከምድርገጽ ጋርቀላቅለውታል ። ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ እንደማይቀር በጌታ የተነገረውም ትንቢት በዚሁ ተፈጽሟል ።

ምስክረ መጻሕፍት ፦

1. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፣ ከአውሳብዮስ ኤጲስ ቆጶስ ዘቄሣሪያ ( በእንግሊዝኛ ትርጉም )

2. የአይሁድ ጦርነት ከዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ( በእንግሊዝኛ ትርጉም )



www.ethiopianorthodox.org

## የቤተሰብ ዓምድ

ከገጽ ፰ የዞረ

በዚህ ሁኔታ ጋብቻዋን የፈጸመችውን የወ/ት ቤዛዊትን ቀደም ያለ መንፈሳዊ ሕይወት ስንመለከት አሁን ካለችበት የተለየ አይደለም የሚያስገርመው « ባልና ሚስት ከአንድ ባህር ይቀዳሉ» እንዲሉ ሁሉ የአቶ የሺጥላም ሕይወት ከእ ትምህርትና ሥርዓት ታንጸ ያደገች ከመሆኗም ሌላ ለማህበሩ በልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች ተሠማርታ የሰራችና አሁንም በመሥራት ላይ ያለች በቤተ ክርስቲያኑም ከሰበካ ጉባኤ ተወካዮች አንድዋ ሆና ስታገለግል የቆየች መሆኑን ከማህበሩ ም/ሊቀመንበር ጠይቀን ተረድተናል ። በዚህ ሁኔታም ለወደፊት የሚኖራት መንፈሳዊ አካሄድና ለቤተ ክርስቲያንም የምትሰጠው አገልግሎት እስከ ሕይወቷ ፍጻሜ ድረስ እንደሚቀጥል ው በተለያዩ ምክንያቶች ፈጽመው የሚርቁ ልጆች አሉና ነው ።

ቤዛዊት ግን ያስደሳች ትዳርን ምሥጢር በሕይወቷ ተርጉማለችና እንደዚህ ከሚባሉት ወጣቶች መካከል እንዷልሆነች መስክራለች ።

እርሷ እንግዲህ ለባሏ ለቤተሰቦቿና ለሌሎችም ሁሉ ታማኝ መሆኗ የማይካድ ነው ሌሎችም በዚህ ሁኔታ ያሉና ለወደፊቱም ኑሮአቸውን በዚህ ሕይወት ለማሳለፍ ያቀዱም አሉ ።

ስለእንደነዚህ ያሉ ሴቶች ሰሎሞንም በ



ሙሽሮቹ የቤተ ክርስቲያኑን ሥነ ሥርዓት ከፈፀሙ በኋላ በምክህ ደናግል ማርያም ወጣቶች መንፈሳዊ መዘምራን ታጅበው ለማረፊያ ወደተዘጋጀላቸው ልዩ ሥፍራ ሲያመሩ ።

ርስዋ ሕይወት የተለየ አለመሆኑ ነው እንግዲህ ከአሁን ጀምሮ የሁለቱ ሕይወት በአንድ ይጠቃለላልና የወ/ት ቤዛይት ሁኔታ ብቻ ቢገለጽ ከአሥር ዓመታት በላይ በቤተ ክርስቲያን አያጠራጥርም ከመጀመሪያው የታነጸውን አካሄድ የኑሮ ሁኔታዎችም ሆኑ የጊዜ ሁኔታዎች ሊያናውጹት አይችሉምና ነው ይኸንን ያልነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ቆይተ ምሳሌው የሚለውን ከመጽሐፈ ምሳሌ 1 ፣ 10 . 31 እናንብ ።

ስለዝግጅቱ ጥያቄ ወይም አስተያየት ካላችሁ በፖ.ሣ.ቁ. 3137 አ.አ ብላችሁ ብትጽፉ ይደርሰናል ።



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የፍልስፍና መፍለቂያ የታሪክ ማኅደር ናት ።

ይህም አባባል ማጋነን ሳይሆን እውነት ስለሆነ ታሪክን ከእነ ተጨባጭ ማስረጃው መመልከት ይጠቅማል በዘፍጥረት 3 ፥19 ላይ በፊትህ ወዝ እንጀራህን አይብላ'' የሚለው ቃል የተገኘው ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከእነቅዱስ ጳውሎስ ከሌሎችም አበው ነው ።

ቤት ንብረት ሚስት ልጅ ያለው ይቅርና ይህ ዓለም ይቅርብን ብለው ዓለሙን መንነው ወደ በረሃ ለገቡት እንኳን በሚያርፉበት ሰዓት ተግባረ እድን እንዲይዙ ማለት ሰሌንና እሱንም የመሳሰሉትን ' የእጅ ሥራዎች እየሠሩ እንዲኖሩ አስተምሮአቸዋል ።

እንግዲህ የምንኩስና ሥራና መሠረቱ በጸሎት ተወስኖ መኖር ብቻ ሳይሆን ተግባረእድንም ይዞ መኖር ነው ። ይህንንም አርአያ የተከተሉ ቅዱሳን አበው ሥራን ከጸሎት ጋር አጣምረው በመያዝ እየተ



ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የትግራይ ሀገረ ስብከት ጳጳስ በአክሱም የቅዱስ ያሬድ ት ቤት ክልል ውስጥ የሚገኘው ቦታ ለልማት እንዲውል በሦስት ጥምድ በሬ ሲያሳርሱ

ብላ ሲል ለአባታችን ለአዳም ከተነገረው ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ በሙሉ ሕይወቱን ከሥራ ጋር አስተባብሮ ይታያል አንዳንድ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን የሰነፎች ቦታ ናት ብለው ሲናገሩ ና ሲዘብቱ ይታያሉ ይኸውም ባለማወቃቸው ቅዱሳት መጻሕፍትን ባለማንበባቸውና ታሪክንም ባለመመልከታቸው ነው እንጂ ቤተ ክርስቲያን ከሠራተኞች በስተቀር ለሰነፎች ቦታ የላትም ። ይህንም መጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው ያስረዳል''የማይሠራ ያለ ሥራ እንዲኖሩ አልተፈቀደም ለማስረጃም ያህል አበ መነኮሳት ለሆኑ ለአቡነ እንጦንዮስ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል የተናገራቸውን እንጠቅሳለን ።

አቡነ እንጦንዮስ ዓለሙን መንነው ከበረሐ ገብተው የሰው ጠላት ዲያብሎስ በተለያዩ ነገሮች ሲፈታተናቸውና መከራንም ሲያጸናባቸው ከቆየ በኋላ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ሕገ ምንኩስናንና በየሰዓቱ ስለሚጸለየው ሥርዓት ጸሎትን ከማስተማሩም በላይ ከጸሎት ጠቀሙ አልፈዋል ።

ዛሬም ቢሆን በየገዳማቱ የሚኖሩ መነኮሳት ይህንን የአቡነ እንጦንዮስ ተግባር በማጥናት ራሳቸውን ችለው ሌሎችንም ድኩማን እየረዱ የሚኖሩ በጥቂቱ የሚገሙቱ አይደሉም ።

አዎ ሥራን ሥራ ያነሳዋልና እግረ መንገዳችንን ጠቀስነው እንጂ ወደ ዓላማችን ''ልማት በቤተ ክርስቲያን'' ወደሚለው ርእሳችን እንመለሳለን ባሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናችን አልፎ አልፎ የልማ



www.ethiopianorthodox.org

ት እንቅስቃሴ በማሳየት ላይ ናት የቤተ ክርስቲያን ደጋፊና ተቆርቋሪ የሆነውም ሁሉ ቤተ ክርስቲያናችን የተለያዩ የሥራ መስኮችን በመክፈት ፍቅርና አንድነት በተሞላበት መንፈስ በሥራ ገሥግሳ ሌሎች የዓለም ዓብያተ ክርስቲያናት ከደረሱበት ደረጃ እንድትደርስ ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግ ላይ ናት ፡፡

በዚህም አንጻር ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የትግራይ ሀገረ ስብከት ጳጳስ በዓለ ሆሣዕና ከመድረሱ ቀደም ሲል ማለት ሚያዚያ 4 ቀን 73 ዓ.ም. አክሱም ጽዮን በመገኘት ከዚያ ቀን ጀምረው እስከ ሆሣዕና ድረስ ልዩ ልዩ ጠቃሚ ሥራዎችን ሲሠሩና ሲያሠሩ ሰንብተዋል ካከናወንዋቸውም ሥራዎች በከፊል እንጠቅሳለን፡፡

1ኛ / የአክሱም እደ ጥበብ ድርጅት ይህ የእደ ጥበብ ድርጅት ቀደም ብሎ በተገኘው ዕርዳታ በአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ስም ተቋቁሞ ከዚአው የሚገኘው ጥቅም ቤተ ክርስቲያኑን ለሚያገለግሉ ካህናት እንዲሆንና ካህናቱም እንደየችሎታቸው እንዲያመርቱበት ታስቦ የተቋቋመ ሲሆን በልዩ ልዩ ምክንያት መሥመሩን ለቆ ከቤተ ክርስቲያን ንብረትነት ወደ ሌላ አቅጣጫ አምርቶ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ጭቅጭቅና ክርክር ተነሥቶ ሳለ ብፁዕነታቸው ከሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች በመነጋገር እንዲመለስ አድርገዋል ፡፡ አሠራሩም ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው መመሪያ እንዲሠራ ሙሉ መብቱና ጥቅሙም የቤተ ክርስቲያን መሆኑን በማሳወቅና በማስረዳት የዕደ ጥበቡ ድርጅት ወደ አክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን እንዲመለስ አድርገዋል 2ኛ በ02 ቀበሌ ለአዲሱ የቅዱስ ያሬድ መንፈሳዊ አዳሪ ት/ቤት ሕንፃ ማሠሪያ የተሰጠው ቦታ ከአሁን ቀደም በሕጋዊ ፕላን በመሐንዲስ የተሰጠ ቢሆንም አዋሳኙ ግልጽ ባለመሆኑ የተለየ ምልክት ከተደረገበት በኋላ ዙሪያውን መሠረት በማስቆፈር መስርተዋል በተጨማሪም ቦታው ለልዩ ልዩ ልማት የሚሆን ስላለው ሥራ ከሚፈታ ለምቶ ከጥቅም መዋል ስላለበት 3 ጥምድ በሬ በማስጠመድ ቦታው ከጥቅም ላይ እንዲውል አድርገዋል ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አስፈላጊ የሆኑትን የአብያተ ክርስቲያናት ጉዳዮች ፈጽመዋል በአርዕስቱ እንደተጠቀሰው ቤተ ክርስቲያናችን የሥራ ፣ የጥበብ እናት እንደመሆንዋ መጠን እኛም ልጆችዋ በፍቅር በሰላምና በአንድነት ሁነን ለሥራ እንታጠቅ በአንድ አሳብ በአንድ ልብም እንሥራ ሥራ የሕይወት ዋስትና ነውና፡፡



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

## ማሳሰብያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ፡፡ ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ፡፡

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org